በኀል ሰከበ፤ በአጽርቅት ተጠብለለ፤ ውስተ ማኅጸነ ድንግል ኀደረ፤ ዮም ተወልደ እግዚእ ወመድኅን ቤዛ ኩሉ ዓለም
(በግርግም ተኛ፤ በጨርቅም ተጠቀለለ በድንግል ማርያም ማኅፀን አደረ፤ የዓለም መድኃኒት ጌታ ዛሬ ተወለደ። )
ቅዱስ ያሬድ

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ መልእክት
፮ ሪፖርታዥ
፱ ቤተ አብርሃም
፲፪ ቃለ መጠይቅ
፲፭ የሕፃናት ዓምድ
፲፯ ትዝብት
፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ


የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
🖂 80078
አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# የጃንሜዳ የጥምቀት በዓል ማክበሪያ ሥፍራ በዓመት ከአንድ ጊዜ በላይ አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ እየተገነባ መሆኑ ተገለጠ

*ምኒልክ ብርሃኑ*

የጃንሜዳ የጥምቀት በዓል ማክበሪያ ሥፍራ በዓመት ከአንድ ጊዜ በላይ አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ እየተገነባ መሆኑን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጠቅላይ ቤተ ክህነት የሕዝብ ግንኙነት መምሪያ ኃላፊ ሊቀ ሥዩማን እስክንድር ወ/ክርስቶስ ገለጹ፡፡

ሊቀ ሥዩማን እስክንድር የ፳፻፲፬ ዓ.ም የጥምቀት በዓል ቅድመ ዝግጅቶችን አስመልክቶ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበራቸው ቆይታ እንዳስታወቁት "የጃንሜዳ የጥምቀት በዓል ማክበሪያ ሥፍራ በዓመት አንድ ጊዜ የጥምቀት በዓልን ብቻ በማሳለፍ እንዳይወሰን የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡ በመሆኑም የማክበሪያ ቦታውን በማስተካከል እና በማዘመን የስብከተ ወንጌል መርሐ ግብራት የሚከናወኑበት፣ ልዩ ልዩ ዝግጅቶች የሚቀርቡበት እና ዓመቱን ሙሉ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ታስቦ እየተገነባ ነው" ብለዋል፡፡

ኃላፊው አክለውም ባለፉት ዐምስት ዓመታት በጠበል ማጠራቀሚያነት አገልግሎት ሲሰጥ የነበረው ገንዳ ውኃውን በከፍተኛ ሁኔታ በማስረግ አገልግሎቱን ያስተጓጉል እንደነበር አስታውሰው "አሁን ላይ ይህንን ችግር ከመሠረቱ ለመፍታት የቤተ ክርስቲያንን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ግንባታ እየተከናወነ ነው" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አያይዘውም "ከዚህ በፊት የገንዳው ቅርጽ ዐራት መዓዘን የነበረ እና የባሕረ ጥምቀቱ አቀማመጥ ወደ ደቡብ አቅጣጫ የዞረ ነበር፡፡ በዚህ ግንባታ ግን ገንዳውን ወደ ክብ ቅርጽ፣ ባሕረ ጥምቀቱን ደግሞ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ለውጥ በማድረግ እየተከናወነ ነው" ያሉት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው በተጨማሪም የጥምቀት በዓል ካለው ሃይማኖታዊ ፋይዳ ባሻገር በማይዳሰስ የዓለም ቅርስነት የተመዘገበ እንደመሆኑ መጠን የማክበሪያ ሥፍራው ውበቱ የተጠበቀ እንዲሆን፣ ካህነትና ምእመናን እንዲሁም ሌላው የበዓሉ ታዳሚ ሁሉ ሥርዓተ ዑደቱን ሳይጨናነቅ



ግንባታው የተጀመረው የጃንሜዳ ታቦታት ማደሪያ የወደፊት ገጽታ

እንዲያከናውን የሚያስችል ቦታ ለማድረግ ታስቦ እየተሠራ ሲሆን ከዚህ በፊት በድንኳን የነበረውን የታቦታት ማደሪያም በማስቀረት ቋሚ የሆነ ማረፊያ እና ዋናው አገልግሎት የሚከናወንበት ዘመናዊ መድረክ መገንባት የጃንሜዳ ዕድሳት አካል ነው" በማለት አስረድተዋል፡፡ ሊቀ ሥዩማን እስክንድር ከዚህ በፊት የጠበል መርጫ መሥመሮች ቁርጥ አነስተኛ በመሆናቸው በርካታ ምእመናን ማየ ጥምቀተ እንደማይደርሳቸው ገልጠው፣ በአሁኑ ሥራ ግን ይህን ችግር መፍታት የሚያስችሉ ዐሥራ ሁለት የጠበል መርጫ መሥመሮች እንደሚኖሩ እና ለሁሉም ምእመናን ተደራሽ እንደሚሆን አስረድተዋል፡፡

በመጨረሻም የ፳፻፲፬ ዓ.ም የጥምቀት በዓልን በበላይነት የሚያስተባብረው የፈረንሳይ ደብር አንቀጸ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል እና በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ የሚመሩ ኮሚቴዎችን በማዋቀር ሥራው መጀመሩን ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም የበዓሉን ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ይዘቶችን የሚዳስሱ ሥነ ጽሑፎች ማሰናዳት፣ ለውጪ ሀገር እንግዶች በእንግሊዘኛ ቋንቋ መጽሔት ማዘጋጀት፣ የክብር እንግዶችን የመቀበል፣ የጃንሜዳ እድሳትን ማፋጠን፣ በተለይም ካለፉት ጊዜያት በተሻለ መንገድ በዓሉን ባማረ እና በደመቀ መንገድ እንዲከበር የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተጠናቀቁ እንደሆነ ከሥራ አስኪያጁ ለማወቅ ተችሏል፡፡



በዘመን ብዛት ያረጀው የካቴድራሉ ከፊል ገጽታ

# ምእመናን ለመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እድሳት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ጥሪ ቀረበ

ካሳሁን ለምለሙ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ለሚገኘው መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እድሳት በመላው ዓለም የሚገኙ ምእመናን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ ማቅረቡን የኢ.ኦ.ቲ.ቤ በዘገባው አስታወቀ፡፡

የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ስላሴ ካቴድራል ዋና አስተዳዳሪ ሊቀ ሥልጣናት ቆሞስ አባ ሲራክ አድማሱ ቤተ ክርስቲያኑ ከተገነባ ጀምሮ ለረጅም ዓመታት ያለምንም እድሳት መቆየቱን መናገራቸውን ከዘገባው መረዳት የተቻለ ሲሆን ጣሪያው ላይ የመሰንጠቅ አደጋ በመድረሱና ውኃ ማፍሰስ በመጀመሩ ሕንጻው ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያኑ ከሚሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎት ባሻገር በቅርስነቱ በርካታ ቱሪስቶች የሚጎበኙት በመሆኑ ለሀገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን ዋና አስተዳዳሪው መግለጻቸውን ዘገባው አመልክቶ ለሀገራቸውና ለወገናቸው ትልቅ ሥራ የሠሩ የሃይማኖት አባቶችና አርበኞች በክብር ያረፉበት በመሆኑ ለቤተ ክርስቲያኑ እድሣት ሁሉም ኢትዮጵያዊ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የካቴድራሉ ሕንጻ እድሳት ዐቢይ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ተድላ ተሾመ በበኩላቸው የቤተ ክርስቲያኑ ሕንጻ ከፍ ባለ ጥራትና በውጭ ሀገር ባለሙያዎች የተገነባ መሆኑን መናገራቸውን ዘገባው አስረድቶ ተገቢ እድሳት ባለመደረጉ ሕንጻው ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰበት መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ካቴድራሉ ካለው ጥንታዊነት የተነሳ እድሳቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ በመሆኑ በዘርፉ ባለሙያዎች ዝርዝር ጥናት መከናወኑን አቶ ተድላ መግለጻቸውን ዘገባው አንስቶ ካቴድራሉ የሕዝብ ሀብትና የሀገር ቅርስ በመሆኑ መላው ኢትዮጵያውያን ለእድሳቱ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ እንዲያደርጉ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡

የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እድሳት ቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኢንጂነር ሥርዓት አየለ ለሚዲያው በሠጡት መግለጫ እንዳስታወቁት ካቴድራሉ ታሪካዊነቱንና ጥንታዊነቱን በጠበቀ መልኩ ለማደስ ከቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር ውይይት መደረጉን ገልጠዋል፡፡

ሕንጻው ጣሪያ ላይ የመሰንጠቅ አደጋ ደርሶበት ውኃ እያፈሰሰ መሆኑና ሌሎች ጉዳቶችን እያስተናገደ መሆኑንን ሰብሳቢው መግለጻቸውን ዘገባው አስረድቷል፤ ስለሆነም ሕንጻው አስቸኳይ እድሳት እንደሚያስፈልገው በጥናቱ መረጋገጡን መናገራቸውን ዘገባው አስረድቷል፡፡

ከእድሳት ሥራው ጋር ተያይዞ የካቴድራሉ ግቢን የማስዋብ ሥራም እንደሚሠራ ሰብሳቢው ማስረዳታቸውን ዘገባው አስታውቆ ሌሎች ወጪዎችን ሳይጨምር ለሕንጻው እድሳት ብቻ ከሰማንያ እስከ አንድ መቶ ሚሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ ያስረዱ ሲሆን ካቴድራሉ በንጉሠ ነገሥት አጼ ኀይለሥላሴ አማካይነት በ፲፱፻፳፬ ዓ/ም ተመሥርቶ ላለፉት ዘጠና ዓመታት አገልግሎት ሲሰጥ መቆየቱን ከካቴድራሉ የተገኘው መረጃ አመልክቷል፡፡

# ድሆችን የቤታችን እንግዳ እናድርጋቸው

መጪው በዓል የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል የምናከብርበት በተለይም በእኛ በኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ዘንድ ልዩ ቦታ የሚሰጠው ከዓበይት የቤተ ክርስቲያናችን በዓላት መካከል አንዱ ሲሆን ልዩ ዝግጅት የሚደረግበት፣ ሰው እና መላእክት አንድ ላይ የዘመሩበት (ሉቃ.፪÷፲፫)፣ ‹‹እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ እጅግ ይደንቃ›› የተባለለት፣ በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል እርቅ የተፈጸመበት ታላቅ በዓል ነው።

ሁሉም ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ለበዓሉ ስለሚያስፈልገውን ቅድመ ዝግጅት መኖሪያ ቤትን ከማጽዳትና ከማስዋብ ጀምሮ ዐዲስ ልብስ በመግዛት፣ የተለያዩ ምግቦችንና መጠጦችን በቤት በማዘጋጀት ለበዓሉ ልይ ትኩረት ይሰጣል። መዋዕለ ጾሙን ጀምሮ በመፈጸም በተለይ ከዋዜማው ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን በመገኘትም የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በፍጹም ደስታ በታላቅ ምስጋና ያከብራል።

ይህ ኦርቶዶክሳዊ ሥርዓት በሁሉም ክርስቲያኖች ዘንድ ልዩ ትኩረት መሰጠቱ፣ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ዶግማና ቀኖና በማያፋልስ መልኩ መደረጉ፤ ይልቁንም በቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ እንደ ቅዱሳን መላእክት ከክርስቶስ ልደት የሚገኘውን ደስታና በረከት ለመካፈል የሚደረገው ትጋት ክርስትናችንን በሚገባ የሚገልጥ መሆኑ ይበል የሚያሰኝ ነው። ነገር ግን ዝግጅቱ ለራስ ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎች አቅመ ደካማዎች ወገኖቻችን አስበን በመርዳት፣ በማልበስ፣ በማብላትና በማጠጣት ሲሆን ደግሞ ይበልጥ የክርስቶስን ቃል ፈጻሚ ክርስቲያኖች ያደርገናል።

በአካባቢያችን ያሉና ባሎቻቸው የሞቱባቸው፣ የሚረዷቸው ልጆች የሌሉአቸውና አቅመ ደካማዎች፣ ያለ ምንም ጧሪና ደጋፊ የቀሩ ወገኖቻችንን በማሰብ እንድንደግፋቸው ክርስትናችን ግድ ይለናል። ሰማይ ዙፋኑ ምድርም የእግሮቹ መረገጫ ስትሆን ስለ ሰው ልጆች ፍቅር መጻተኛ በመሆን ማደሪያ አጥቶ በበረት የተገኘውን፣ በጨርቅ የተጠቀለለውን ጌታ በማሰብ በዓሉን ስናከብር ከነዚህ አጉራሽና አልባሽ ወገን ከሌላቸው ድሆችና ጦም አዳሪዎች ጋር ማሳለፍ በክርስትናችን ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ተግባር ነው። እንደነዚህ ዓይነቶቹን አቅመ ደካሞች አረጋውያን ቤታቸውን ብናጸዳላቸው፣ ልብሶቻቸውን ብናጥብላቸው፣ የሚበሉትን አዘጋጅተን ብንሰጣቸው ባጠቃላይ ካለን ላይ ብናካፍላቸው የወንጌልን ቃል እንፈጽማለን። የወንጌልን ቃል መፈጸም ደግሞ የአባቴ ብሩካን ተብለን እንድንመሰገንና በቀኙ እንድንቆም ያደርገናል።

ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ ‹‹ ንጹሕ የሆነ፣ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር ዘንድ ይህ ነው፤ ወላጆች የሌሉአቸውን ልጆች፣ ባልቴቶችንም በችግራቸው መጠየቅ፣ በዓለምም ከሚገኝ ርኵሰት ሰውነትን መጠበቅ ነው›› (ያዕ.፩÷፳፯) እንዳለ በዚህ በዓል እንዲህ ዓይነት ወገኖችን ማሰብ እና በሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ መርዳት በረከት ነውና ይህ በረከት ሊያልፈን አይገባም።

በዚህ ታላቅ የደስታ ቀን ለምግብ እንኳ ለሥራ ያልደረሱ በዚያውም ላይ አሳዳጊ የሌላቸውን የጎዳና ላይ ሕፃናት እንዲሁም ድሆችንና ጦም አዳሪዎችን ወደ ቤታችን በመውሰድ የቤታችን እንግዳ አድርገን በዓሉን አብረን ብናሳልፍ በዓሉን በቤታችን ከክርስቶስ ጋር አብረን ስላሳለፍን ደስታችን ፍጹም በረከታችንም ብዙ ነው።

ስለሆነም በዚህ የበዓል ወቅት እንደዚህ አይነቶቹን አሳዳጊ የሌላቸው የጎዳና ሕፃናት፣አልባሽ አጉራሽ የሌላቸውን ድሆችና ጦም አዳሪዎች ከጎዳና ላይ አንሥቶ የሕፃኑን የክርስቶስን በዓል አብሮ ማክበር የሁላችንም ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ግዴታችን ነው። አንዳንድ ብንካፈል እንኳ የማይዳረሱንን ሕፃናት፣ ድሆችና አቅመ ደካሞች የሚያስፈልጋቸውን ሰጥቶ ማስደሰት፣ ሰው እንደሆኑም እንዲያስቡ ማስቻል ለማኅበራት፣ ለተለዩ

በጎ አድራጊ ግለሰቦች ብቻ የሚተው ሳይሆን የሁላችንም ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ግዴታ መሆኑን አውቀን ራሳችንን ለዚህ የበረከት ሥራ ማዘጋጀት ይጠበቅብናል፡፡

**በዚህ ታላቅ የደስታ ቀን ለምግብ እንጂ ለሥራ ያልደረሱ በዚያውም ላይ አሳዳጊ የሌላቸውን የጎዳና ላይ ሕፃናት እንዲሁም ድሆችንና ጦም አዳሪዎችን ወደ ቤታችን በመውሰድ የቤታችን እንግዳ አድርገን በዓሉን አብረን ብናሳልፍ በዓሉን በቤታችን ከክርስቶስ ጋር አብረን ስላሳለፍን ደስታችን ፍጹም በረከታችንም ብዙ ነው፡፡**

በዚህ የበዓል ወቅት በአብሮ መብላት ባህላዊ ዕሤቶቻችን ውስጥ የሚወዱንን ከመውደድ፣ ለሚሰጡን ብቻ በመስጠት ይልቅ ብድር ሊመልሱልን የማይችሉትን በቤታችን በመጥራት ልናለብሳቸው፣ ቤታችን ያፈራውን ማዕዳችንንም ልናጋራቸው ይገባል፡፡ ስለዚህ በቅዱስ ወንጌል ‹‹. . . ተርቤ አላበላችሁኝም፣ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝም፣ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝም፣ . . . .›› (ማቴ. ፳፭፥፴፩—፵፮) ተብሎ እንደተጻፈ የተራቡትን ማብላት፣ የተጠሙትን ማጠጣት፣ የተራቆቱትን ማልበስ፣ እንግዶችን መቀበል፣ የታሠሩትን መጠየቅ እንድንፈጽማቸው በክርስቶስ የተሰጡን ትእዛዛት ናቸውና ይልቁንም በዚህ ጊዜ የተቸገሩትን አብዝተን መርዳት ይጠበቅብናል፡፡

አንዳንዶች እንደሚመስላቸው ደግሞ የተቸገሩትን መርዳት ያለብን ከተረፈን ላይ ብቻ ሳይሆን እንደ ድኃዋ መበለት (ሉቃ.፳፩፥፬) ያለንን በመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም ያለኝ ትንሽ ነው፣ በእኔ አቅም የትኛውን ቀዳዳ መሸፈን እችላለሁ ብሎ ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ ከኛ በታች ሆነው የሰውን ርዳታ በመሻት እጃቸውን ለሚዘረጉ ወገኖቻችን ምላሽ መስጠት ይገባል፡፡ እኛ የምንችለውን የመጨረሻዋን ትንሽ ነገር በማድረግ እንደ መጀመሪያው ዘመን ክርስቲያኖች ማንኛውም የተቸገረ ወገን በመካከላችን እንዳይኖር ማድረግ ነውና ክርስትናችንን በተግባር መተርጎም ይጠበቅብናል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ የጌታችን የመድኃኒታችን የልደት በዓል፣ በዙሪያችን የሚገኙትን፣ ጎዳና ላይ የወጡትን በየቤቱ የኑሮ ውድነት ከአቅማቸው በላይ ሆኖ የዕለት ጉርስ መጉረስ ያቃታቸውን አረጋውያንን በፍቅር ዐይን በማየት መንከባከብ፣ የጎደላቸውን ነገር ተመልክቶ ማሟላት ይገባናል፡፡ በዚህ የተቀደሰ በዓል የታመሙትን በመጠየቅ፣ የታሠሩትን በመጎብኘት የጽድቅ ሥራ ልንሠራ ይገባል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አንዱ ሌላውን የመደገፍ፤ አንዱ ሌላውን የመርዳት መንፈሳዊ ዕሤትም በዓልን ጠብቆ የሚደረግ ብቻ ሳይሆን በየዕለት ኑሯችን፣ በየዕለት ሕይወታችን ልንተገብረው የሚገባ ልምድም መሆን አለበት እንላለን፡፡

# ተፈናቃይ ወገኖች የቤተ ክርስቲያንም ሆነ የመንግሥት ያልተቋረጠ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል!

ካሣሁን ለምለሙ

ሀገራችን ኢትዮጵያ በውስጥና በውጭ ጠላቶች በተለያዩ ዘመናት በተለያዩ ሁኔታዎች ስትፈተን መቆየቷን የተለያዩ ድርሳናት ሕያው ምስክሮች ናቸው። የውጭ ወራሪና የውስጥ ባንዳ ተባብረው ሀገራችንን ከታሪኳ ዝቅ ለማድረግ፣ ከክብሯ ለማውረድና አንድነቷን ለመናድ ያልፈነቀሉት ድንጋይ ያልቧጠጡት ቋጥኝ የለም። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ቸርነት ከብረት የጠነከረ አንድነት ባላቸው ልጆቿ አማካይነት የውሥጥ ሆነ የውጭ ጠላቶቿን እንዳመጣጣቸው ስትመልስ መቆየቷ ታሪክ ምስክር ነው። የውሰጥ ባንዳዎችም የውጭ ጠላቶቻችንን መንገድ እየመሩ፣ ሥልት እየቀየሱና ተላላኪ እየሆኑ ባገለገሉበት የመከራ ወቅት ዘመን የማይበግራቸው የቁርጥ ቀን አርበኞች የኢትዮጵያ ልጆች የውጭ ወራሪን አሳፍረው፣ ባንዳንም ቀብረው አሳይተዋል። ለዚህም ጣሊያን፣ ግብፅ፣ ሱዳን /ድርቡሽና/ ሶማሊያ የውርደትና የሽንፈት ምሳሌዎች ናቸው።

አሁንም ፳፻ኛው ክፍለ ዘመን "ኢትዮጵያ ተዳክማለች፤ሕዝቦቿ ተከፋፍለዋል፤ አንድነቷ ፈርሷል፤ ሀገሩን ሊከላከል የሚችል ትውልድ የለም" ብለው ያሰቡ የሀገራችን ጥንተ ጠላቶች በአራቱም አቅጣጫ እንደቆዳ ወጥረዋታል። ምዕራባውያንና አንዳንድ የኢትዮጵያን እድገትና አንድነት የማይፈልጉ የአፍሪካ ሀገራት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከአንድ ዓመት በላይ የዘለቀውን የአንድ እናት ልጆች ጦርነት እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሀገራችንን ለመከፋፈል፣ ለመውረርና፣ በሞግዚት ለማስተዳደር፣ አንድነቷንና ሉዓላዊነቷን ለመናድ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ።

ጦርነቱ ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ በሰውና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከተለ ሲሆን በተለይ መተኪያ የሌለው በርካታ የሰው ሕይወት ጠፍቷል፣ በሀገራችን ኢትዮጵያ በሚከሠቱ የእርስ በእርስ ጦርነቶችም ሆነ ከውጭ ወራሪዎች ጋር በሚደረግ ጦርነት ሁሉ ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን የመጀመሪያ የመከራ ገፈት ቀማሾች ናቸው። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተነሣው ጦርነትም የበርካታ አብያተ ክርስቲያናት ቅርሶች ተዘርፈዋል፤ በቃጠሎ ወድመዋል ፤እንዲሁም በርካታ ምእመናንና አገልጋዮች ያለኃጢያታቸው ተገድለዋል፤ ቆስለዋል፤ አካባቢያቸውንም ጥለው ተሰደው የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ አጥተዋል። ለተፈናቃዮች፣ ለሃይማኖት ተቋማትና ለማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት መንግሥትና ግለሰቦች የሚሠሩት የመልሶ ማቋቋም ሥራ ቢኖርም በቂ አይደለም።

**ማኅበሩ የቤተ ክርስቲያን ጉዳት፣ የካህናት ለሞት መዳረግ፣ የምእመናን ሞትና ስደት አሳስቦት የአስቸኳይ ጊዜና የመልሶ ማቋቋም ኮሚቴ አዋቅሮ በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱን የቀረበው ሪፖርት ያትታል።**

ውድመት የደረሰባቸው ምእመናንም ሆኑ ተቋማት ወደ ቀደመ ሁኔታቸው አልተመለሱም። የወደሙ አብያተ ክርስቲያናትንና ንዋየ ቅድሳትን መተካትና ለተፈናቀሉ ወገኖችንም የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ሁሉ በማድረግ ቶሎ ወደ አካባቢያቸው ተመልሰው የተለመደ ሕይወታቸውን እንዲመሩ ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህ ወቅት በርካታ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትና አህጉረ ስብከት ለተፈናቃዮች መልሶ ማቋቋሚያ የሚውል የገንዘብ ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ። ይህ የሚበረታታ ተግባር ቢሆንም ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ወገኖች ጸንተው እስኪቋቋሙና ወደ ቀያቸው እስኪመለሱ ድረስ ያልተቋረጠ የቤተ ክርስቲያንም ሆነ የመንግሥት ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል።

**በዚህ ደጋፍም ማኅበሩ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት የኅብረተሰብ ክፍሎችን የዓይነት ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዳደረገ በሪፖረቱ አስታውቆ ድጋፉን የተለየ የሚያደርገው የሃይማኖት ልዩነት የሌለበት መሆኑ ነው ብሏል።**

ግለሰቦች፣መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ለተፈናቃሉ ወገኖች ከሚያደርጉት ርብርብ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን የተደረገለትን የርዳታ ጥሪ ተከሎ በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ ቦታዎች ለተፈናቃሉ ወገኖች ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል። ማኅበሩ ከሚሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎት በተጨማሪም በማኅበራዊ ድጋፍ ዘርፍ ሲሳተፍ ይህ የመጀመሪያው አይደለም። ምንም እንኳን ማኅበሩ የተመሠረተበት ዓላማ ወንጌልን ለመላው ዓለም ማዳረስ ቢሆንም ሀገርና ወገን በተቸገሩ ወቅት የማይታጠፍ እጅ እንዳለው ይታወቃል።

የተቸገሩትን መረዳት፣ ያዘኑትን ማጽናናት፣ የታሠሩትን መጠየቅ፣ የታረዙትን ማልበስ፣ የተጠሙትን ማጠጣትና የተራቡትን ማብላት አንዱ የወንጌል ትሩፋት ነውና። በዚህ መሠረት ማኅበረ ቅዱሳን በጦርነቱ ምክንያት ተፈናቅለው በሸሸት ከደሴና አካባቢው፣ ከኮምቦልቻ፣ ማጀቴ፣ አጣዬና ሸዋ ሮቢት በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በደብረ ብርሃን ከተማ ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያ ተጠልለው ለሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከኅዳር ፲፱ ቀን ፳፻፲፬ እስከ ኅዳር ፳ ቀን ፳፻፲፬ ዓ/ም ድረስ የዓይነት ድጋፍ ማድረጉን ማኅበሩ ባቀረበው ሪፖርት መረዳት ተችሏል። ማኅበሩ የቤተ ክርስቲያን ጉዳት፣ የካህናት ለሞት መዳረግ፣ የምእመናን ሞትና ስደት አሳስቦት የአስቸኳይ ጊዜና የመልሶ ማቋቋም ኮሚቴ አዋቅሮ በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱን የቀረበው ሪፖርት ያትታል።

ከሪፖርቱ መረዳት እንደተቻለ በድጋፉ ሕፃናት፣ አረጋውያን፣ ነፍሰጡሮች፣ አጥቢ እናቶች የተለያየ የጤና ችግር ያለባቸው ወገኖችም በይበልጥ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል።

በደብረ ብርሃን መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም፣ በደብረ ኤባ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተጠልለው ለሚገኙ ከተለያዩ ማእከላትና ወረዳ ማእከላት ተፈናቅለው ለመጡ ለአብነት መምህራንም፣ ለግቢ ጉባኤ አባላትና ከኦሮሚያ ክልል ተፈናቅለው ለመጡ ወገኖች ሁሉ ድጋፍ እንደተደረገላቸው ከሪፖርቱ መረጃ ለማወቅ ተችሏል። በዚህ ደጋፍም ማኅበሩ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት የኅብረተሰብ ክፍሎችን የዓይነት ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዳደረገ በሪፖረቱ አስታውቆ ድጋፉን የተለየ የሚያደርገው የሃይማኖት ልዩነት የሌለበት መሆኑ ነው ብሏል።

ማኅበሩ ከደብረ ብርሃን ማእከል ጋር በጋራ የመረጃና የሥርጭት ሥራዎችን የሠራ ሲሆን በዚህ የተቀደሰ ተግባር ድጋፍ የተደረገላቸው ኦርቶዶክሳውያንን ጨምሮ የሌላ እምነት ተከታዮችም ለተደረገላቸው ድጋፍ ምስጋና ማቅረባቸው በሪፖረቱ ተመልክቷል።

ለተፈናቃዮች የተደረገላቸው ድጋፍ ቁሳዊ ጥቅም ብቻ ሳይሆን የመንፈስ ርካታ እንዲያገኙ ማድረጉን የገለጠው ሪፖርቱ ተፈናቃዮች ጊዜያዊ የምግብ ፍጆታ እንዲያገኙ ከማድረጉ ባሻገር አባላት ለማኅበራቸው የተለየ ፍቅር እንዲኖራቸውና ምእመናንም ማኅበሩ ማን እንደሆነ ግንዛቤ የጨበጡበት መሆኑን ሪፖርቱ አስረድቷል።

በደብረ ብርሃን ጊዜያዊ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያ ተጠልለው ለሚገኙ ተፈናቃዮች የተደረገው የዓይነት ድጋፍ ከአንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ ብር በላይ ወጭ የተደረገበት ሲሆን ከብዙ ተፈናቃዮች መካከል በጣም ለተቸገሩ ወገኖች ተደራሽ መሆኑን ሪፖርቱ አስረድቷል።

# ማኅበሩ ሰብሳቢና አሳዳጊ የሌላቸው ሕፃናት መሠረታዊና ማኅበራዊ ፍላጎት እንዲሟላላቸው ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል

*ካሳሁን ለምለሙ*

***በኢትዮጵያ የበጎ አደራጎት ድርጅቶችና የማኅበራት ታሪክ ውስጥ ለሀገርና ለወገን የማይረሳ አሻራ ያሳረፉና እያሳረፉ ያሉ በርካቶች ናቸው:: በዚህ መሠረት በዘመናችን በቁጥር ጥቂት የማይባሉ ማኅበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ተመሥርተው አቅማቸው የፈቀደውን አገልግሎት እየፈጸሙ ይገኛሉ:: አንዳንዶቹ በሃይማኖታዊ የአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በሀገራዊና ማኅበራዊ ዘርፎች የተሰማሩ ናቸው:: አንዳንዶቹ በተቋቋሙለት ዓላማ ልክ ሥራዎችን ሲሰሩ ሌሎች ደግሞ ከተቋቋሙለት ዓላማ ውጭ በሆነ መንገድ ሲንቀሳቀሱ ይስተዋላሉ:: እንደነዚህ ዓይነት ደርጊቶች የሚስተዋሉት ማኅበራት ወይም ድርጅቶች የተቋቋሙለትን ዓለማ ካለማወቃቸው የመነጨ ወይም ሆን ብለው የራሳቸውን ሀብትና ዝና ለማሳደግ የሚጠቀሙ ናቸው::***

***ወደ ተሳሳተ መንገድ ከሚሄዱት ማኅበራት ይልቅ ሀገርንና ወገንን እየጠቀሙ ለሚገኙት ዋጋና ዕውቅና መስጠት መልካም ነው:: ከዕውቅናም ወደ በጎ ሥራ ለመሰማራት በሀገራችን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ህልውና ዋናው ደረጃ ምዝገባ ሲሆን ድርጅቱ ወይም ማኅበሩ በሕግ ፊት ዕውቅና የሚያገኝበት በመሆኑ ካሉት ደረጃዎች ውስጥ ወሳኝ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል:: አንድ ድርጅት ወይም ማኅበር በተመዘገበ ጊዜ ሕጋዊ ሰውነት አግኝቶ በሕግ ፊት ውጤት ያላቸውን ተግባራት ለማከናወን ብቁ ይሆናል:: በሌላ አባባል አንድ በመመሥረት ላይ የነበረ ድርጅት ወይም ማኅበር ሲመዘገብ ውል መዋዋልን ጨምሮ የሕግ ትርጉም ያላቸውን ተግባራት ማከናወን ይችላል:: ለአንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማኅበር ሠራተኞችን በመቅጠር እና ክንውኖችን በመተግበር የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈፀም የሚያስችል ብቃት በሕግ ፊት ያስገኝለታል ማለት ነው:: የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማኅበሩ በሕግ በተቀመጡ ምክንያቶች ካልፈረሰ በቀር ሕጋዊ ሰውነቱን ይዞ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል::***

***በመሆኑም የአቡነ ዜና ማርቆስ የሕፃናትና የአረጋውያን መርጃ ማኅበር በመንግሥት ሕጋዊ ሰውነት አግኝቶ ለዐሥራ ሁለት ዓመታት ያህል ሕፃናትንና አረጋውያንን ሲረዳ ቆይቷል፣ እየረዳም ይገኛል:: ይህን የበጎ አድራጎት ማኅበር የዚህ እትም የቤተ አብርሃም እንግዳ አድርገናል:: መልካም ንባብ::***

አቡነ ዜና ማርቆስ የሕፃናትና አረጋዊያን መርጃ ማኅበር በጻድቁ አባታችን በአቡነ ዜና ማርቆስ ስም የተሰየመ ሲሆን ጻድቁ አባታችን በ፲፫ኛው መቶ ክ/ዘመን የነበሩ ኢትዮጵያዊ አባት ናቸው:: ጻድቁ አባታችን በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች እየተዘዋወሩ የእጅ ሥራን፣ ፍቅርን፣ መረዳዳትንና በሥርዓት መኖርን እያስተማሩ የኖሩ ኢትዮጵያዊ አባት ናቸው:: በዘመናቸው የተቸገረ በመርዳታቸው ለሰው ልጆች ሁሉ የፍቅርና ደግነት አርአያ ሆነዋል:: ይህ ደግ ሥራቸው ‹‹የድሆች አባት›› የሚለውን ስያሜ አስገኝቶላቸዋል:: ለሀገርና ለወገን መልካም ያደረጉትን የእኒህን ጻድቅ አባት ሥራዎች ለመዘከርና አርአያነታቸውንም ለመከተል በማሰብ የማኅበሩ ስያሜ አቡነ ዜና ማርቆስ ተብሏል::




ማኅበሩ ኃላፊነት በሚሰማቸውና ችሎታውም ባላቸው ጽኑ ኢትዮጵያውያን በጎ አድራጊዎች ሰኔ ፳፻፪ ዓ.ም. የተቋቋመና በኢትዮጵያ የበጐ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ የተመዘገበ የበጎ አድራጎት ማኅበር ነው:: የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር ባወጣው አዋጅ ቁጥር ፲፩፻፲፫/፳፻፲፩ዓ.ም መሠረትም አገር በቀል ድርጅት ሆኖ በኤጀንሲው ቁጥር ፲፰፻፵ በዳግም ምዝገባ ተመዝግቧል:: አቡነ ዜና ማርቆስ የሕፃናትና አረጋውያን መረጃ ማኅበር እያንዳንዱ ሰው የተቸገሩ ሕፃናትና አረጋውያንን የኑሮ ሁኔታ የማሻሻል ኃላፊነትና ችሎታ አለው በሚል ጽኑ እምነት ላይ ተመስርቶ የተቋቋመ ማኅበር ሲሆን ሁሉም ኃላፊነቱን ለመወጣት ቢተጋ በሌሎች ሰዎች ሕይወት ላይ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል የሚያምን ግብረ ሠናይ ማኅበር ነው::

አቡነ ዜና ማርቆስ የሕፃናትና አረጋውያን መርጃ ማኅበር የራሱ የሆነ ራእይ ያለው የበጎ አድራጎት ድርጅት ሲሆን ራእዩም ሕፃናትና ወላጆቻቸው ሁለንተናዊ አቅማቸው ጎልብቶ ለማኅበረሰቡ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አበርክተው እንዲሁም አረጋውያን ለኑሮ የሚያስፈልጋቸው ተሟልቶላቸው ማየት ነው። ማኅበሩ ሕፃናትና አረጋውያን የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍና እንክብካቤ ያገኙ ዘንድ የቤተሰቦችን፣ የሕፃናትና የአረጋውያንን አቅም የመገንባት ተልእኮ አለው። ማኅበሩ ‹‹ሁሉም ዜጋ የተቸገሩ ሕፃናትንና አረጋውያንን ኑሮ ለማሻሻል ማገዝ አለበት›› የሚለውን የጋራ የኃላፊነት ባህል በማሥረፅ ራእዩን ለማሳካት እየሠራ ያለ ነው።

**ጻድቁ አባታችን በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች እየተዘዋወሩ የእጅ ሥራን፣ ፍቅርን፣ መረዳዳትንና በሥርዓት መኖርን እያስተማሩ የኖሩ ኢትዮጵያዊ አባት ናቸው። በዘመናቸው የተቸገረ በመርዳታቸው ለሰው ልጆች ሁሉ የፍቅርና ደግነት አርአያ ሆነዋል። ይህ ደግ ሥራቸው ‹‹የድሆች አባት›› የሚለውን ስያሜ አስገኝቶላቸዋል።**

ሕፃናት ተገቢውን እንክብካቤ ከቤተሰቦቻቸው ካገኙ ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ሆነው ያድጋሉ። በከባድ የድህነት ቀንበር ሥር የሚኖሩ ቤተሰቦች ግን በአብዛኛው የልጆቻቸውን ፍላጎት በተመለከተ በቂ ግንዛቤ ላይኖራው ይችላል፤ ጥቂት ግንዛቤ ቢኖራቸውም፣ ለልጆቻቸው ማስተማሪያ የሚሆን ገንዘብ አይኖራቸውም። በተጨማሪም እኒህ ቤተሰቦች ትምህርት ድህነትን ለማጥፋት ያለውን ጠቃሚነት ላይረዱት ይችላሉ፤ቢኖራቸውም ፍላጎታቸውን ለማሟላትና ልጆቻቸውን ለመንከባከብ በቂ ሀብት አይኖራቸውም። ይህንንም ግምት ውስጥ በማስገባት የአቡነ ዜና ማርቆስ የሕፃናትና አረጋውያን መርጃ ማኅበር ወላጆች የራሳቸውን ኑሮ በትክክል ለመምራትና ልጆቻቸውንም እንዲደግፉ የሚያስችሉ መረጃዎችንና ክህሎትን የሚያስጨብጡ ልዩ ልዩ ተከታታይ ሥልጠናዎችን ለወላጆች ይሠጣል።

ከዚህም በተጨማሪ ወላጆች ለመሠረታዊ የዕለት ፍጆታቸው፣ ለልጆቻቸውም ለዘለቄታ የሆነ የትምህርት የሚረዳቸው የገቢ ማስገኛ ሥራ ውስጥ እንዲሠማሩ ለማስቻል መነሻ ካፒታል የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል። የሕፃናቱን የትምህርት ተደራሽነትና የትምህርት ተሳትፎ ለማረጋገጥ ይረዳ ዘንድ ወላጆች እስከሚበቁና ልጆቻቸውን መረዳት እንደሚችሉ እስኪረጋገጥ ቀጥተኛ የገንዘብ ድጋፍም ያደርጋል፤ በተጨማሪም የምግብ፣ የሕክምና፣ የትምህርት ቁሳቁስ (የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ፣ ደብተር፣ ወዘተ) የማጠናከሪያ ትምህርት አገልግሎት ወጭ ድጋፍ ይሠጣል፣ በሥነ ልቡናም አስፈላጊ የሆነውን ድጋፍና ክትትል ሁሉ ያደርጋል።

በእርጅናና በበሽታ ምክንያትም ራሳቸውን መንከባከብ የማይችሉ ሰዎችን ለመንከባከብ የሚያስችል ሥርዓት በሀገሪቱ ውስጥ በበቂ ሁኔታ ባለመዘርጋቱ ምክንያት ቤተሰብ የሌላቸው አረጋውያንና የአካል ጉዳተኞች አሳዛኝ በሆነ የብቸኝነት ኑሮ ለመኖር ይገደዳሉ። ለሀገሪቱ እድገትና ብልጽግናም አሁን ያለውን ትውልድ በመልካም ስብእና በመቅረጽ አስተዋጽኦ ያደረጉ አረጋውያንን ማኅበረሰባችን የመንከባከብ ኃላፊነት አለበት ብሎ ማኅበሩ ያምናል። ከዚህ በተጨማሪም ዕድሉ ከተሰጣቸውና አጋጣሚው ከተመቻቸላቸው አረጋውያኑ ለኅብረተሰቡ የሚያደርጉትን ታሪክ የመንገር አስተዋጽኦ መቀጠል ይችላሉ ብሎም ያምናል። በዚህ እምነቱ በመነሣትም ለአረጋውያኑ ወርኃዊ የምግብ አበል፤ የቁሳቁስና የሕክምና ድጋፍ፣ ወርኃዊ የግኙነት መርሐ ግብር ያዘጋጃል የሞራል ድጋፍም

ይሰጣል፤ እንዲሁም የቤት ለቤት ጉብኝት በማድረግ አረጋውያኑን ይንከባከባል።

በአጠቃላይ በማኅበሩ በኩል ፫፻፴፰ ወንዶችና ፫፻፳፯ ሴት ሕፃናት በድምሩ ፯፻፩ሕፃናት ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። እንዲሁም ፲፩ አባቶችና ፫፻፳፬ እናቶች በድምሩ ፫፻፴፰ ወላጆች ሥልጠናና የገንዘብ ድጋፍ አግኝተው ወደ ሥራ ገብተዋል። ከነዚህም ውስጥ ፪፻፳፱ ወላጆች ራሳቸውን የቻሉ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የማኅበሩን የገንዘብ ድጋፍ የማይፈልጉ ናቸው። ፻ አረጋውያንና አረጋውያት (፳፯ ወንዶችና ፸፫ ሴቶች) የገንዘብ፣ የቁሳቁስ የሕክምናና የሥነ ልቡና ድጋፍ አግኝተዋል። የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ ፫ ጥቃቅንና አንስተኛ ማኅበራት ማደራጃ ማኅበሩ ላቋቋማቸው ሦስት የወላጅ ማኅበራት የመሥሪያ ቦታና ሥልጠና ሰጥቷቸዋል። እነዚህም ማኅበራት ፹፱ ወላጆች የታቀፉባቸው ናቸው። በአሁኑ ወቅት እነዚህ ወላጆች በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ በመሳተፍ ይገኛሉ። በአጠቃላይ በማኅበሩ የሚረዱ ፲፯ ሕፃናት በትምህርታቸው ጥሩ ውጤት በማምጣታቸው ምክንያት ከተለያዩ የግል ትምህርት ቤቶች የነጻ የትምህርት እድል አግኝተዋል። አቡነ ዜና ማርቆስ የሕፃናትና አረጋውያን መርጃ ማኅበር የወላጆችን አቅም የመገንባት፣ ለሕፃናቱ ትምህርት ተደራሽነት የማስፋትና አረጋውያንን የመንከባከብ ሥራውን አጠናክሮ የመቀጠል ዕቅድ አለው።

ማኅበሩ በቀጣይ ለወላጆች የኑሮ ማሻሻያ ክህሎት ሥልጠና ለመስጠት የሚያግዝና የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን ለመጀመር ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ማሰባሰብ ሥራ እቅድ አውጥቶ ይጠይቃል። ለአብነት ለአንድ ወላጅ ሥራ ማስጀመሪያ ከስምንት ሽህ ብር በላይ ያስፈልጋል። ለሕፃናቱ ትምህርትና የኑሮ መደጎሚያ የሚውል የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የሕክምና ድጋፍ የሚውል ገንዘብ ለማሰባሰብም በመጪው የበጀት ዓመት የተጠናከረ ሥራ ይሠራል።

የአቡነ ዜና ማርቆስ የሕፃናትና አረጋውያን መርጃ ማኅበር ሕፃናትና ወላጆቻቸው ሁለንተናዊው አቅማቸው ጎልብቶ ለማኅበረሰቡ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ሲያበረክቱ፣ ለአረጋውያንም ለኑሮ የሚያስፈልጓቸው ነገሮች ሁሉ ተሟልተውላቸው ሲደሰቱ ማየት ይፈልጋል። ማኅበሩም ሕፃናትና አረጋውያን የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍና እንክብካቤ ያገኙ ዘንድ የቤተሰቦችን፣ የሕፃናትና የአረጋውያንን አቅም የመገንባት ተልእኮ አለው። ተልእኮውንም ከግብ ለማድረስ ሕፃናት ሁለንተናዊ ፍላጎቶቻቸው ተሟልተው በአካልና በአእምሮ የጎለበቱ ብቁ ዜጎች እንዲሆኑ ተግቶ ይሠራል። የትምህርት እድል ያላገኙ ሕፃናት የትምህርት እድል እንዲያገኙ ያመቻቻል። ሰብሳቢና አሳዳጊ የሌላቸው ሕፃናት መሠረታዊና ማኅበራዊ ፍላጎታቸው እንዲሞላላቸው ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። (ለምሳሌ፡- የምግብ ልብስ መጠለያ፣ሕክምና፣ የትምህርት መረጃ መሣሪያ፣ ቦርሳ፣ የጽዳት መጠበቅና ሌሎች ተጨማሪ ድጋፎች) የሚደረግላቸው የሕፃናት ወላጆችም (አሳዳጊዎች) በዘለቄታ ራሳቸውን እንዲችሉ በተለያየ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች እንዲሠማሩ ማስቻል ዋነኛ ዓላማ ሲሆን አረጋውያንና አቅመ ደካሞች ክብር ያለው ሕይወት እንዲኖሩም ለማድረግ ይተጋል። ማኅበሩ ለአረጋውያንና አቅመ ደካሞች የኅብረተሰብ ክፍሎች የምግብ፣ የአልባሳት፣ የህክምና እና የጽዳት መጠበቂያ ግብዓቶችን የሥነ- ልቡና እና ማኅበራዊ ድጋፍ ጭምርም እንዲገኙ እደረገ ይገኛል።

**ወላጆች እስከሚበቁና ልጆቻቸውን መረዳት እንደሚችሉ እስኪረጋገጥ ቀጥተኛ የገንዘብ ድጋፍም ያደርጋል፤ በተጨማሪም የምግብ፣ የሕክምና፣ የትምህርት ቁሳቁስ (የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ፣ ደብተር፣ ወዘተ) የማጠናከሪያ ትምህርት አገልግሎት ወጭ ድጋፍ ይሠጣል፣ በሥነ ልቡናም አስፈላጊ የሆነውን ድጋፍና ክትትል ሁሉ ያደርጋል።**

# “ማኅበሩ ተረጂዎች ከልመና ወጥተው በዘላቂነት ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን እንዲረዱ የሚያግዝ ነው”

**አቶ ስማችው ሺበሺ**
**(የአቡነ ዜና ማርቆስ የሕፃናትና አረጋውያን መርጃ ማኅበር የቦርድ ሰብሳቢ)**

*ካሣሁን ለምለሙ*

ከብዙ ዘመናት ጀምሮ በሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ መንፈሳዊና የበጎ አድራጎት ማኅበራት ተመሥርተው ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ሰጥተዋል:: መንፈሳዊ ማኅበራቱ ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንን የተመለከቱ መንፈሳዊ ተግባራትን እየከወኑ የመጡ ሲሆን በአንጻሩ የበጎ አድራጎት ማኅበራት ደግሞ ሀገራዊና ማኅበራዊ ሥራዎችን እየሠሩ ያሉ ናቸው:: ማኅበረ ቅዱሳንን ጨምሮ በርካታ ማኅበራት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የጀርባ አጥንት ሆነው በማገልገል አባላቱ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆችና ተተኪ አገልጋይነታቸውን አስመስክረዋል:: የበጎ አድራጎት ማኅበራቱ እንዲሁ ሀገርንንና ወገንን በማለዳ ካገለገሉ በኋላ ዕድሜ ያከበራቸውን  ወገኖች ሰብስቦ የዕለት ጉርስ በማጉረስና የዓመት ልብስ በማልበስ በፍቅርና በጸጋ የሚያኖሩ ናቸው:: በዚህ ሂደት ውስጥም በርካታ ወላጆቻቸውን ያጡና ወላጆቻቸው ጥሩ የሆነ የኢኮኖሚ አቅም የሌላችው ሕፃናት፣ወላጆች፣ጧሪና መጦሪያ የሌላቸው አረጋውያንና ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ ሆነዋል::

ከእነዚህ በጎ አድራጎት ማኅበራት መካከል ደግሞ ሕፃናትንና አረጋውያንን በመርዳትና በመንከባከብ የሚታወቀው አቡነ ዜና ማርቆስ የሕፃናትና አረጋውያን መርጃ ማኅበር አንዱ ነው:: ማኅበሩ በፍቅርና በርዳታ በሚታወቁት በጻድቁ አቡነ ዜና ማርቆስ ስም የተሰየመ ሲሆን ከምሥረታው አንሥቶ ለዐሥራ ሁለት ዓመታት ያህል አረጋውያንንና ሕፃናትን እንዲሁም ወላጆችን በመንከባከብና በመርዳት አሳልፏል:: አሁንም ድረስ በመንከባከብና በመርዳት ላይ ይገኛል:: ማኅበሩ ሰሞኑን ለአራት ተከታታይ ዓመታት በንግድና በተለያዩ የሙያ መስኮች ያሠለጠናቸውን ወላጆች ታኅሣሥ 09 ቀን 2014 ዓ/ም ለሦስተኛ ጊዜ በላፍቶ ሞል ባስመረቀበት ወቅት ዝግጅት ክፍላችን ተገኝቶ ከማኅበሩ የቦርድ አባል ከሆኑት ከወ/ሮ ዘውድነሽ አሰፋ እና ከወቅቱ የቦርድ ሰብሳቢ ከሆኑት ከአቶ ስማቸው ሽበሽ ጋር አጭር ቆይታ አድርጓል:: ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል:: መልካም ንባብ::

**ስምዐ ጽድቅ፡- የማኅበሩ ጠቅላላ አገልግሎት ምን እንደሆነ ቢነግሩኝ?**

**ወ/ሮ ዘውድነሽ አሰፋ፡-** ማኅበሩ የተቋቋመበት ዓላማ የተቸገሩ ወገኖችን አፈላልጎ ለመርዳትና ለመደገፍ ሲሆን በዚህ የድጋፍ መርሐ ግብርም እናቶች፣ አባቶች፣ ሕፃናትና አረጋውያን ተጠቃሚዎች ናቸው:: በዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ የሚገኙ ሰዎች ራሳቸውን ከድህነትና ከተኅሳቀለ ኑሮ



አቶ ስማቸው ሺበሺ
የአቡነ ዜና ማርቆስ የሕፃናትና አረጋዊያን መርጃ ማኅበር የቦርድ ሰብሳቢ

እንዲያላቅቁ ማኅበሩ የተቻለውን ሁሉ እያደረገ ያለ ነው:: በችግር ላይ ያሉ ወገኖች ራሳቸውን በኑሮ እንዲደጉሙና የራሳቸውን ሥራ እንዲሠሩ ማኅበሩ የሐሳብና መጠነኛ የገንዘብ ድጋፍ ያደርግላቸዋል:: ማኅበሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ በመሆን ለተረጂዎች ለሥራቸው የሚያግዟቸውን ሥልጠናዎችን እንሰጣለን::

ተረጂዎች ሥልጠናቸውን በሚወስዱበትም ወቅት ልጆቻቸው እንዳይቸገሩ ከትምህርት ቁሳቁስ  በተጨማሪ ለምግብ የሚያግዛቸውን በየወሩ የአራት መቶ ብር ድጋፍ

ይደረግላቸዋል፡፡ ማኅበሩ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የሃይማኖትና የብሔር ልዩነትን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ እውነተኛ መረጃን መርምሮ የሚረዳ ነው፡፡ በጣም የተቸገሩ ወገኖችን ለመለየት ከየቀበሌያቸው የሚገኘውን እውነተኛ መረጃ ይጨምራል፤ በተጨማሪ ለበርካታ ወራት በጎረቤቶቻቸውና በሚያውቋቸው ሰዎች አማካይነት ጥናት አድርጎ የልየታና የመረጣ ሥራ ይሠራል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በመረጣ ሂደት ላይ የማይገባው ሰው የድርጅቱን ድጋፍ ሊያገኝ ስለሚችል በተደጋጋሚ የማጣራት ሥራ ይሠራል፡፡ ማኅበሩ ተረጂዎችን በዘላቂነት በመደገፍ ከልመና ወጥተው ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን እንዲረዱ ያግዛል፡፡ በአዲስ አበባ ባሉ አንዳንድ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ ተረጂዎች በማኅበሩ አማካይነት እገዛ ተደርጎላቸው መልካም ሕይወት የሚመሩና አርአያ የሚሆኑ አሉ፡፡

ወላጆች ከሥልጠና በኋላ ለሥራ መጀመሪያ የተወሰነ ገንዘብ ይሰጣቸውና ከዚያ በኋላ የሚሰጣቸው ገንዘብ ይቆምና ሥራ በሚጀምሩበት ወቅት የምክር አገልግሎትና የሐሳብ ድጋፍ ብቻ ይደረግላቸዋል፡፡ ድጋፍ የሚደረግላቸው አካላት ከተደረገላቸው ድጋፍ በኋላ በየወቅቱ ያሉበት ሁኔታ ክትትል ይደረጋል፡፡ ማኅበሩም ለችግረኛ ወገኖች ድጋፍ የሚያደርገው ከተለያዩ ግለሰቦችና ድርጅቶች፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ከሚገኘው በጎ አድራጊ ወገኖች ከሚያገኘው ድጋፍ ነው፡፡ የማኅበረ ቅዱሳን አባላትን ጨምሮ ሌሎች ወገኖችም ለማኅበራችን በቋሚነትና በጊዜያዊነት ድጋፍ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በዋናነት ማኅበሩን በቋሚነት የሚደግፍት ግን የማኅበሩ መሥራች አባሎቻችን ናቸው፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ለተረጂዎች የሚሰጠው ሥልጠና ምን ዓይነት ነው?**

**ወ/ሮ ዘውድነሽ፡-** ለእናቶች(ለተረጂዎች) የሚሰጠው ሥልጠና በሙያቸውና በፍላጎታቸው መሠረት ሲሆን መነገድ የሚፈልጉ ከሆነ ለንግድ ሥራ የሚያግዛቸው ሥልጠና ብቻ ይሰጣቸዋል፤ ሙያዊ ሥራዎችን መሥራት ለሚፈልጉ ደግሞ የሹራብ ሥራ፣ የምግብ ዝግጅትና ሌሎች የተለያዩ ሙያዊ ሥልጠናዎች ይሰጣቸዋል፡፡

በዚህ መሠረት የሹራብ ሥራዎችንና ሌሎች ሙያዎችን ጨምሮ ሠርተው የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ሕይወት ቀይረዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ በምግብ ሥራና በሌሎች ንግድ ሙያዎች ተሰማርተው እየሠሩ ያሉ ሠልጣኞች አሉ፡፡ ከአካባቢው የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር በመነጋገርም ልዩ ልዩ ሼዶች (የመሥሪያ ቦታዎች) ይዘጋጅላቸዋል፡፡ በንግድም ሆነ በሙያዊ ሥራ ያላቸው ውጤታማነትና ትርፋማነት በየጊዜው ይገመገማል፤ መልካም ሥራው እንዲጎለብት፣ ድክመቱ ደግሞ እንዲታረም ይደረጋል፡፡ ተረጂዎች በየፍላጎታቸው ለሥራ ይሰማራሉ፡፡ ለሥራ እንዲያግዛቸው ደግሞ በመጀመሪያ ሁለት ሺህ ብር የሚሰጣቸው ሲሆን የሥራ ተነሳሽነታቸውና ቁርጠኝነታቸው ታይቶ ደግሞ ስምንት ሺህ ብር ይጨመርላቸዋል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ተረጂዎች የሙያም ሆነ የክህሎት ሥልጠና ከወሰዱ በኋላ ማኅበሩ የሚያደርግላቸው እገዛ ምንድን ነው?**

**ወ/ሮ ዘውድነሽ፡-** ከላይ እንደተገለጸው ለተረጂዎች የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ ከሥልጠና ጀምሮ ራሳቸውን ችለው ሥራ እስከሚጀምሩበት ጊዜ ድረስ ነው፡፡ በሥራቸው ሂደት ሁሉ ማኅበሩ ሁለንተናዊ ክትትልና ድጋፍ ያደርግላቸዋል፡፡ በማኅበሩ በኩል የሚረዳ አንድ ሰው ቢያንስ ለአራት ዓመታት ያህል ያልተቋረጠ ክትትልና ድጋፍ ያገኛል፡፡ በእነዚያ አራት ዓመታት ውስጥ ተረጅዎቹ (ሠራተኞቹ) የደረሱበትን ሁኔታ ሁሉ ለማኅበሩ ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡ በቀረበው ሪፖርት መሠረት ማኅበሩ አስፈላጊውን የገንዘብም ሆነ የምክር አገልግሎት ይሰጣቸዋል፡፡ የተለያዩ የውይይት መርሐ ግብሮችም ይዘጋጃሉ፤ በመርሐ ግብሩ ላይ የተለያዩ ሐሳቦች ተነሥተው ውይይት ይደረግባቸዋል፤ የልምድ ልውውጥም ይካሄዳል፡፡ በሚደረገው የሐሳብ ልውውጥ ወቅት ተረጂ ወላጆች ችግራቸውን በግልጽ ያስረዳሉ፣ ከችግሩ መነሻነትም ማኅበሩ አስፈላጊውን ሁሉ እገዛ ያደርጋል፡፡ የተረጂዎቹን ችግር ማኅበሩ ካጠና በኋላም በድጋሚ ሌላ አዲስ ሥራ የሚጀምሩበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- እስካሁን ድረስ በማኅበሩ ምን ያህል ወገኖች የድጋፍ ተጠቃሚ ሆኑ?**

**አቶ ስማቸው ሽበሽ፡-** ማኅበሩ ሕጋዊ ዕውቅና አግኝቶ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ሰባት መቶ አንድ ሕፃናትን በወላጆቻቸው በኩል ድጋፍ እያደረገ አስተምሯል፡፡ ሦስት መቶ እናቶችን ደግሞ የሙያ፣ የንግድ ሥራና ሥልጠና የገንዘብ ድጋፍ አድርጎላቸው፣ ወላጆች የባንክ አካውንት ከፍተው የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ገንዘብ እየቆጠቡ በኢኮኖሚ እንዲያግዙ ማኅበሩ የሥልጠና እገዛ አድርጓል፡፡

የሥራ ተነሳሽነት እንዲኖራቸውም ድጋፍ ያደርጋል፡፡ አረጋውያንን ተመለከተ እስካሁን ድረስ አንድ መቶ ሁለት አረጋውያንን ረድቷል፡፡ ከእነዚህ መካከል የተወሰኑት በሕይወት የሌሉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በአሁኑ ሰዓት ከቤተሰቦቻቸው ጋር እየኖሩ እገዛ የሚደረግላቸው ናቸው፡፡ ዛሬ ሠልጠነው የተመረቁ ወላጆች ሲጨመሩ በአጠቃላይ እስከ ዛሬ ድረስ ከአራት መቶ ሃምሳ በላይ የሰለጠኑና የተረዱ ሲሆን የሕፃናቱ ቁጥር ደግሞ ከአንድ ሺህ በላይ ሆኗል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በዛሬው ዕለት ሥልጠናቸውን አጠናቀው የተመረቁ ወላጆች ምን ያህል ናቸው?**

**አቶ ስማቸው:-** በዛሬው ዕለት ሰማንያ ሦስት ወላጆች የተሰጣቸውን ሥልጠና በትጋት አጠናቀው የተመረቁ ሲሆን እነዚህ ወላጆች ላለፉት አራት ዓመታት የተለያዩ ሥልጠናዎችን የወሰዱ ናቸው:: ሥልጠናው የሙያና የክህሎት ሥልጠናዎችን ያካተተ ሲሆን በተለይ በንግድ ዘርፍና በእደ ጥበብ ዙሪያ ያጠነጠነ ነው:: ሥልጠናውን በሚገባ ተከታትለው ካጠናቀቁ በኋላ ለንግድ ሥራ የሚያግዛቸውን መነሻ ገንዘብ ማኅበሩ ይሰጣቸዋል:: በንግድ ሂደቱ ላይ ወላጆች የሚያስመዘግቡት ለውጥ እየታየ የሁለተኛ ዙርና የሦስተኛ ዙር የገንዘብ ድጋፍም ይደረግላቸዋል:: ከተከታታይ የገንዘብ ድጋፍ በኋላ የድጎማ ገንዘብ ይሰጣቸውና ከድጋፍ በራቀ ሁኔታ ራሳቸውን ሕይወታቸውን እንዲመሩ ይደረጋል:: ይህ ማለት ግን የገንዘብ ድጋፍ ይቀራል ማለት ነው እንጂ የሚያገኙት ሌላ ድጋፍ ይቀራል ማለት አይደለም::

ከዚያም በኋላ ወላጆች በየክፍለ ከተማው በማኅበር ተደራጅተው የጠነከሩት የደከሙትን እያበረቱ በጋራ የሚሠሩበት እድል ይፈጠራል:: የቁጠባ ባህላቸውም እንዲያድግ እርስ በርሳቸው ይደጋገፋሉ:: የገቢ ምንጭ ሊያስገኝላቸው ከሚችሉ ግብረ ሠናይ ድርጅቶች ጋር የማስተሳሰር ሥራም ይሠራል:: ይህ የጀመሩት የንግድም ሆነ የእደ ጥበብ ሥራ ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲሸጋገር ያግዛቸዋል:: በማኅበሩ እገዛ ከፍተኛ ደረጃ ከደረሱ ወላጆችም ማኅበሩን በተለያየ ሁኔታ ከማገዝ ባሻገር ልጆቻቸውን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ እያስተማሩ ይገኛሉ:: ልጆቹም በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ገብተው እንዲማሩ ማኅበሩ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቶላቸዋል:: በአጠቃላይ ማኅበሩ ልጆች ላይም ሆነ ወላጆች ላይ የእችላለሁ መንፈስ ፈጥሯል:: በዛሬው ዕለት ለአራተኛ ጊዜ የተመረቁት ወላጆት ጊዜው ፈትኗቸው በብዙ መከራ ውስጥ ያለፉ ነበሩ:: ዛሬ ግን በሥልጠና ታግዘው ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ከዛም አልፎ ማኅበሩን ለመርዳት ዝግጁዎች ሆነዋል::

**ስምዐ ጽድቅ:- ማኅበሩ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? በቀጣይስ የት ቦታ ልናገኘው እንችላለን?**

**አቶ ስማቸው:-** የማኅበራችን ባለድርሻ አካላት የምንላቸው በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ ያሉ የሚመለከታቸው የሥራ ሂደት ክፍሎችና በፋይናንስና ኢኮኖሚ ሚኒስትር ጽ/ቤት ያሉ አካላት ናቸው:: በእነዚህ መሥሪያ ቤቶች ያሉ አካላት ለማኅበሩ ሕጋዊ ማኅበራዊ ድጋፍ ያደርጋሉ:: ከእነዚህ መሥሪያ ቤቶች በተጨማሪ በጎ አድራጊ ግለሰቦችና ድጅቶች የማኅበሩ ባለድርሻ አካላት ናቸው:: ሌላውና ዋነኛ የማኅበሩ ባለድርሻ አካላት የምንላቸው ደግሞ የማኅበሩ መደበኛ አገልጋዮች ሲሆኑ በተለይ ማኅበራዊ አገልጋዮቹ በእያንዳንዱ ተረጅ ጓዳ ውስጥ ዘልቀው በመግባት የሚሠሩት ሥራ ከፍተኛ ነው:: እነዚህ አካላት ሙያቸውንና ራሳቸውን ሰጥተው እያገለገሉ ያሉ ናቸው:: ያለ ባለድርሻ አካላት ማኅበሩ አሁን ያለበት ቦታ ሊደርስ አይችልም ነበር:: ባለድርሻ አካላቱ ከዕውቀታቸውም በተጨማሪ የአይነትና የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋሉ:: አሁን ባለው መረጃ መሠረት ማኅበሩ በየወሩ እስከ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር ወጭ ያደርጋል:: ይህንን ወርኃዊ ወጪ ውጭ ሀገር የሚኖሩ የማኅበሩ አባላት ይሸፍኑልናል::

እነዚህ አካላት ድጋፍ የሚያደርጉልን በምንረዳቸው ወላጆች ወይም ሕፃናት ልክ ነው:: ለእያንዳንዱ ሕፃን በየወሩ ሰባት መቶ ኀምሳ ብር ተቆራጭ እናደርጋለን:: የእናቶች የሥራ መጀመሪያ በጀትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው:: በቀጣይ ስድስት ዓመታት ለአንድ ወላጅ ለሥራ ማስጀመሪያ የሚሆን ሦስት ሺህ ብር ያስፈልገናል ብለን በእቅድ አስቀምጠናል:: የተረጂ ሕፃናትን ቁጥርም በቀጣይ ወደ አንድ ሺህ ለማሳደግ አቅደናል:: አሁን ያለው የተረጂ ሕፃናት ቁጥር አራት መቶ ብቻ ነው:: ይህንን እቅድ እውን ለማድረግ የገንዘብ ችግር ከፍተኛ ማነቆ ቢሆንብንም ተጨማሪ የገቢ ምንጮችን የምናፈላልግ ይሆናል:: ለሚቀጥሉት ስድስት ዓመታት ብቻ ከሰማንያ ሚሊዮን ብር በላይ በጀት ያስፈልገናል:: ይህንን ለማግኘት ማኅበሩ ቋሚ የሆነ የገቢ ምንጭ እንዲኖረው የተለያዩ ፕሮጀክቶች አዋጭነታቸውን አረጋግጠን የምንሠራ ይሆናል:: የሚሠራው ፕሮጀክት በአንድ በኩል ተረጂን የሚያግዝ በሌላ በኩል ደግሞ የማኅበሩን የዕለት ከዕለት ሥራ የሚያግዝ ይሆናል::

**ስምዐ ጽድቅ:- ቀረ የሚሉነት ነገር ካለ?**

**አቶ ስማቸው:-** ማኅበሩን በመደገፍ ታላቅ ዋጋ እንድናገኝ በልዩ ልዩ መንገድ መሳተፍ ተገቢ ነው:: በገንዘብ፣ በዓይነትና በሙያ ማኅበሩን መደገፍ ያስፈልጋል:: በማንኛውም ሁኔታ ማኅበሩን ለመደገፍ የሚፈልጉ አካላት ሁሌም ቢሆን በራችን ክፍት ነው:: ማኅበሩ እዚህ ደረጃ ድረስ የኢኮኖሚ ተጎጂዎችን እንዲረዳ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ያሉ አካላት የራሳቸውን ሕይወትና ኑሮ ትተው ነው:: ከራስ በፊት ለወገን ብለው ዋጋ በሚከፍሉ ሰዎች የቆመ ማኅበር መሆኑን በመረዳት የማኅበሩን አቅም ከዚህ በላይ የተሻለ ለማድረግ ርብርብ ማድረግ ያስፈልጋል:: ለዚህ ተግባር ደግሞ ሁሉም ሰው የበኩሉን አስተዋጽኦ ቢያደርግ መልካም ነው:: ማኅበሩ እስከ ክፍለ ከተማ ድረስ የተሸለመና ለሌሎች ማኅበራት አርአያ የሆነ ነው:: ያለምንም ደመወዝ ማኅበሩን የሚያገለግሉ እንዳሉ በመረዳት የኢኮኖሚ አቅም የሌላቸው ተረጂዎች ሕይወታቸው እንዲሻሻል በጋራ መሥራት ያስፈልጋል::

**ስምዐ ጽድቅ:- ለነበረን ቆይታ በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ::**

**ወ/ሮ ዘውድነሽ አሰፋ /አቶ ስማቸው ሽበሽ/:-** እኛም እናመሰግናለን!

# የገና በዓል እና የገና ጨዋታ

ምኒልክ ብርሃኑ

ሰላም ለእናንተ ይሁን ልጆች! እንደምን አላችሁ? እግዚአብሔር ይመስገን እኛ በጣም ደኅና ነን፡፡ እንኳን ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል በሰላም አደረሳችሁ! እንኳን አብሮ አደረሰን እንደምትሉ እርግጠኞች ነን፡፡

ልጆች! ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ቀን የገና በዓል ወይም የልደት በዓል በመባል ይታወቃል፡፡ ገና ቃሉ የግሪክ ልደት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በዛሬ ቆይታችን ስለገና በዓል እና አባቶቻችን የገና በዓልን ለምን እንደሚያከብሩ እንማራለን ማለት ነው፡፡

ልጆች! የገና በዓል ከዘጠኙ የጌታችን ዐበይት በዓላት መካከል አንዱ ነው፡፡ በዓሉን የምናከብረው ደግሞ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ፣ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ የተወለደበትን ዕለት መታሰቢያ በማድረግ ነው፡፡

ልጆች! ጌታችን የተወለደው በቤተልሔም ከተማ በከብቶች በረት በመጀመሪያው ዓመተ ምሕረት ታኅሣሥ ሃያ ዘጠኝ ቀን ነው፡፡ እኛ ክርስቲያኖች ይህንን የተወለደበትን ታኅሣሥ ሃያ ዘጠኝ ቀን ምክንያት በማድረግ በየዓመቱ የጌታችን የመድኃታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል እናከብራለን ማለት ነው፡፡ ይህ በዓል ደግሞ በሀገራችን ኢትዮጵያ ቅዳሴ እና በዝማሬ፣ በምስጋና እና በታላቅ ደስታ ድምቀት ይከበራል፡፡

ልጆች! እናንተስ የገናን በዓል እንዴት ነው የምታከብሩት? መቼስ የገና ዛፍ በመሥራት፣ ዛፉ ላይ ደግሞ መብራት፣ ብልጭልጭ በማድረግ እንደማትሉ እናምናለን፡፡ ልጆች! የገና ዛፍ በመሥራት የገና አባት እያሉ የሚያከብሩት ፈረንጆች እንጂ እኛ ኢትዮጵያውያን አይደለንም፡፡

የገና ዛፍ እና የገና አባት ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል ጋር የሚያገናኘው ምንም የክርስትና አስተምህሮ የለውም፡፡ እንዲሁም ከኢትዮጵያውያን ባህልና ትውፊት ጋር የሚያገናኘው አንዳች ነገርም የለም፡፡ እኛ ደግሞ የራሳችን ባህል፣ ታሪክ እና ማንነት ያለን ሕዝብ በመሆናችን ከሁሉም አስቀድመን የራሳችን ባህል ማስጠበቅና ማክበር ይገባናል፡፡ ስለዚህ ከዚህ ቀጥለን ኢትዮጵያውያን የገና በዓልን እንዴት እንደሚያከብሩ እንማራለን፡፡ በጥሞና ተከታተሉን፡፡

ልጆች! በሀገራችን ኢትዮጵያ በዓላት በተለያዩ ዝግጅቶች ይከበራሉ፡፡ በዝማሬ፣ በመብል፣ በመጠጥ፣

በደስታ እንዲሁም በጨዋታ ይከበራል፡፡ በይበልጥ ደግሞ በበዓላት ጊዜ የሚዘወተሩ የጨዋታ ዓይነቶች አሉ፡፡ ታዲያ እነዚህ ጨዋታዎች መንፈሳዊ ይዘትና ሃይማኖታዊ መሠረት ያላቸው ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል የገና ጨዋታ አንዱ ነው፡፡

ልጆች! የገና ጨዋታ ተጫውታችሁ ታውቃላችሁ? የገና ጨዋታ ከጌታችን ልደት በዓል ጋር ተያይዞ የሚዘወተር የጨዋታ ዓይነት ነው፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ የገናን ጨዋታ የሚጫወቱት እረኞች ብቻ ነበሩ ይባላል፡፡ ይህም እረኞች ጌታችን ሲወለድ ከሁሉም ቀድመው በማየት ከመላእክት ጋር የደስታ መዝሙር ስላቀረቡ እና በጌታ መወለድ ደስ ስለተሰኙ ነው፡፡




ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተወለደ

የገና ጨዋታ ለመጫወት የሚያስፈልጉ ነገሮች በትር (ዱላ) እና ሩር ናቸው፡፡ በትር ከሥሩ ጠፍጣፋ ተደርጎ በጌጥ የሚከረከም እና በጨዋታ ግዜ እንዳይሰበር ከጠንካራ እንጨት የሚቀረጥ የዱላ ዓይነት ነው፡፡ ሩር ደግሞ ድቡልቡል ቅርጽ ያላት እንደኳስ ክብ

የሆነች መጫወቻ ናት። የምትዘጋጀውም ከእንጨት ወይም ከዛፍ ሥር ነው።

ከዚያም ልጆች! ሁለት ቡድኖች ተቧድነው ሰፋ ባለ ሜዳ ላይ በትራቸውን ይዘው ይገባሉ። ታዲያ የገና ጨዋታ ከመጀመሩ በፊት ሩርዋ ዓመቱን ሙሉ ከተቀመጠችበት ከወጣች በኋላ የአገር ሽማግሌዎች መርቀው ጨዋታውን ያስጀምራሉ። እያንዳንዱ ቡድን ሩርዋን በመለጋት የማሸነፍያ ድንበር ለማሳለፍ ጥረት ይደረጋል። ጥረቱ ተሳክቶ ድንበሩን ያሳለፈ አሸናፊ ይሆናል ማለት ነው።

የገና ጨዋታ የራሱ ሆነ ሕግ ያለው ሲሆን ተጫዋቾቹ ከጨዋታው በፊት ምግብ በትንሹ በልተው ነው የሚመጡት። ይህም ደግሞ በጨዋታው ወቅት እንደልባቸው መሮጥ እና መንቀሳቀስ እንዲችሉ፤ ብዙ በልተው ሲሮጡ ደግሞ ሆዳቸውን እንዳያመቸው ነው። ይህ ካልሆነ ግን በልቶ ጠጥቶ መሮጥ አቅቶት ተሸናፊ ይሆናል።



ልጆች የገና ጨዋታ ሲጫወቱ

ልጆች! ይህን የገና ጨዋታ ለየት የሚያደርገው አንድ ነገር አለ። እርሱም በገና ጨዋታ ጊዜ የሚጫወቱት ሰዎች የዕድሜ ገደብ የሌላቸው መሆኑ ነው። ከትልቅ እስከ ትንሽ፣ ከእረኛ እስከ ዳኛ፣ ከጌታ እስከ ሎሌ፤ ልጆች፣ ወጣቶች፣ አባቶች አንድ ላይ አብረው ይጫወታሉ። ሌላው ቀርቶ የቤተ መንግሥት ሰዎች ንጉሡም፣ መኳንንቱም፣ መሳፍንቱም ከሕዝቡ ጋር አንድ ላይ ይጫወታሉ። በዚህ ምክንያት "በገና ጨዋታ የለም ሎሌ የለም ጌታ" የተባለው።

ደግሞም የገና ጨዋታ ስንጫወት ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። ምክንያቱም ሳናውቅ በዱላ ልንመታታ እንችላለን። ሆኖም ግን ልጆች! በዱላ ተመታሁ፣ እግሬ ተሰበረ ብሎ ማልቀስ፣ መሳደብ፣ ቂም በቀል መያዝ አይቻል። ምናልባትም ከእኛ በዕድሜ ከፍ ከሚሉ ትላልቅ ሰዎች ጋር ብንጫወትም እንኳ ሩሩን ለመምታት ስንል ብንመታቸው አይቆጡንም፤ አይመቱንም። ምክንያቱም የገና በዓልን የምንጫወተው የጌታችንን ልደት እያሰብን፣ በዓሉን ለማክበር ስለሆነ ነው። ለዚህ ነው "በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ" የሚባለም ለዚሁ ነው።

ልጆች! የገና ጨዋታ በጌታችን ልደት ወቅት መከወኑ የራሱ የሆነ ምሳሌና ምሥጢር አለው። በትሩ የጌታችን ምሳሌ ሲሆን ሩሩ ደግሞ የሰይጣን ምሳሌ ነው። ምሥጢሩ ደግሞ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ አድረጎ የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ ወደዚህ ምድር እንደመጣና በሩር የተመሰለውን ሰይጣንን እንደቀጠቀጠው የሚያሳይ ጨዋታ ነው።

አያችሁ አይደል ልጆች! ቀደም ብለን እንዳነሣነው እኛ ኢትዮጵያውያን ባህሎቻችን ሃይማኖታዊ ትርጉም ያላቸው ናቸው። በዚህም መሠረት የገና ዛፍ እና የገና አባት የኛ ባህል እና መንፈሳዊ ይዘት የሌለው መሆኑን ተረድተናል ማለት ነው።

ስለዚህ በገና በዓል ጊዜ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚገኙ ልጆች ሁልጊዜ የገናን ጨዋታ ይጫወታሉ። እናንተም ከሰፈር ጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን፣ በገና በዓል ጊዜ ዛፍ ከመሥራት ይልቅ የገና ጨዋታ መጫወት አለባችሁ። ደግሞም በዱላ እንዳትመታቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባችኋል።

በሉ ልጆች! ለዛሬ በዚህ ይብቃን፤ በሚቀጥለው እስከምንገናኝ መልካም የገና በዓል እንዲሆንላችሁ እንመኛለን።

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**

***ምንጭ፡- ባህልና ክርስቲያናዊ ትውፊት በኢትዮጵያ፤ ካህሳይ ገ/እግዚአብሔር፤ ገጽ 213-215፤ ማኅበረ ቅዱሳን፤ 2010 ዓ.ም.***

# መልካም መዓዛና ውበት ለቅጽረ ቤተ ክርስቲያን

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

ውብ አድርጎ አንድን ነገር መሥራት ማዘጋጀትን የተማርነው ከእግዚአብሔር ነው:: ‹‹ነገርን ሁሉ በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው›› (መክ. ፫፥፲፫) እንደተባለ:: እግዚአብሔር ከሠራውና ካደረገው ሁሉ ውብ ያልሆነ አንዳች ነገር የለም:: እጅግም የሚደነቅ ውበትን በእርሱ ሥራ ውስጥ እናያለን::

እግዚአብሔርም ይህን ለሰዎች ሲሰጥም ውብ እና የተደነቀውን በመስጠት ፍቅሩን አሳይቷል:: እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከፈጠረ በኋላ እንዲኖሩበት ያዘጋጀው ሥፍራ ኤደን ገነት ታላቅ ስጦታ እንደነበር የምናስተውለው እጅግ የተዋበ ሥፍራ ስለነበረ ነው:: ኤደን ገነትና በውስጡ ያለው ሁሉ የውበት ማንፀሪያ ሆኖ የሚያገለግል ነው:: ‹‹በጫፎቹም ብዛት ውብ አደረግሁት በእግዚአብሔር ገነት በኤደን የነበሩ ዛፎች ሁሉ ቀኑበት›› (ሕዝ ፴፩፥፱) እንዲል::

ገነት ውብ የሆነ ለሽልማትም የተዘጋጀ፤ የተከበረም ሥፍራ ነው:: በዚያም እግዚአብሔር የሚመላለስበት፣ ሰዎችንም የሚያነጋግርበት ነበር:: ‹‹የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ›› (ዘፍ ፫፥፰) እንደተባለ:: ስለሆነም በዚህ ሥፍራ አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን አነጋግረዋል:: አመስግነዋል:: ስለዚህ ይህ ሥፍራ ውብ ሆኖ የተዘጋጀ ስለሆነ የጸሎትም፣ የምስጢር መገለጫም፣ የመሥዋዕትም ሥፍራ ነበር ማለት ነው::

ነገር ግን ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ በተላለፈ፣ ራሱንም በበደለ ጊዜ መጀመሪያ ያጣው ይህን ውብ ሆኖ የተዘጋጀ ያማረ ሥፍራ ነበር:: ‹‹ከገነት አስወጣው፤ የተገኘበትንም መሬት ያርስ ዘንድ›› (ዘፍ ፫፥፳፫):: ስለዚህ ገና አርሶም፣ ለፍቶም ወደሚጠቀምበትና ወደሚያዘጋጀውም ሥፍራ ተባረረ:: ከዚህ የምንረዳውም እግዚአብሔርና ሰው በቅርብ የሚገናኙበት ሥፍራ የተዋበ፣ የሚበጅና የሚጠበቅ ሥፍራ ሊሆን እንደሚገባ ነው::

ንጉሥ ሰሎሞንም ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙበትን ቤተ መቅደስ ባሠራ ጊዜ እጅግ ያማረና የተዋበ ለማድረግ መትጋቱን ከታሪኩ እንረዳለን:: ቤተ መቅደሱን ያስውበዋል፤ ያሳምረዋል፤ ሥርዓትም ያስይዘዋል:: የበለጠ ለማሳመርም ያለውን ምርጥ ነገር ሁሉ ተጠቅሟል:: በምድር ላይ አለ የተባለ የጢሮስ ጠቢብ ኪራምን ለሥራው አስመጥቷል:: ለሥራው ያስፈልጋል ያለውን የጢሮስ ቁሳቁስና ማዕድን ሁሉ አስቀረቧል:: አፀዱን ከአበቦች ከማስጌጥ ጀምሮ እስከ ውስጥ ቅድስተ ቅዱሳኑ ድረስ በምድር ላይ እጅግ በጣም ጥሩ የተባለ ወርቅን ሁሉ አስነጥሮ ሠርቷል:: እግዚአብሔርም ስለሚወድ እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚጎበኝበትን፣ ሕዝቡም የፈጣሪን ፊት የሚፈልግበትን ሥፍራ አስውቦታል:: ይህ ታላቅ ሥራ የተደነቀ መሆኑን ንግሥተ ሳባ ከምድሯ መጥታ ባየችው ሁሉ መደነቋን መስክራለች ‹‹ባየች ጊዜ ነፍስ አልቀረላትም›› (፩ኛነገ. ፲፥፭)::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለጸሎት የመረጠው ሥፍራ ጌቴሴማኒ የተባለው የአትክልት ሥፍራ ነበር:: በዚያም መሠረት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አብያተ ክርስቲያናትን ሲያንጹ አፀዱ እንዲያምርና አካባቢው ውብ እንዲሆን የተለያዩ ዕፅዋቶችንና አትክልቶችን ይተክሉ ነበር::

አፀደ ቤተ ክርስቲያን ለቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ጤናማ አየርን፣ በጎ መዓዛን፣ መልካም ገጽታን በመስጠት ክብርን ያጎናጽፋል፤ ለምእመናንም መልካም መስሕብ ይሆናል:: ግሩም መዓዛ ካለው ከመቅደሱ የዕጣን መሥዋዕትም ጋር ምእመናን በዚያ እንዲቆዩ፣ ዕረፍት እንዲሰማቸው፣ ቃለ እግዚአብሔርንም ለመስማት የሚያስችል መረጋጋት እንዲጎናጸፉ ያደርጋል:: በጸሎት የመመሰጥ ጊዜም ፍጡራን በማስተዋል ፈጣሪን ለማክበር ዕድል ይሰጣቸዋል:: ቤተ ክርስቲያንም ማርጀት፣ መቆሸሽ፣ መሻከር፣ መምረር ሊገልጻት ለማይችል መንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ሆና ትታሰባቸዋለች:: መንግሥተ ሰማያት

የተዋበች፣ የተዘጋጀች ሽልማት ነችና:: ‹‹ቅድስቲቱ ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባሏ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ›› (ራዕ ፳፩፥፪)

ለእግዚአብሔር መሥዋዕት፣ ጸሎት፣ ምስጋና፣ ስእለት፣ ዝክር… የሚደረግበት፤ ካህናት የሚተጉበት፣ ምእመናን ሁሉ በጉባኤ የሚታደሙበት፣ ቃለ እግዚአብሔር የሚነገርበት ሥፍራ ሁሉ ያማረና የሰመረ ሲሆን ለሥጋም ለነፍስም ደስ ያሰኛል:: ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ነገር ሁሉ ከንጽሕና ጋር ሲሆን እጅግ ደስ ያሰኛል:: ይልቁንም ለነፍሳቸው ንጽሕና የሚጨነቁ ሰዎች ደግሞ ሰነፎች አይደሉም፤ ትጉኃን ናቸው እንጂ:: ስለዚህ በአፀደ ሥጋ ሳሉ አገልግሎት የሚሰጡበትና የሚቀበሉበት ሥፍራ ሁሉ ንጹሕና ያማረ እንዲሆንም ይተጋሉ:: የትጉኃን ቤት ቤተ ክርስቲያንም ሁልጊዜ ንጹህ፣ ውብና በጎ መዓዛ ያላት ሆና መገኘት አለባት::

አሁን፣ አሁን በአንዳንድ አጥቢያዎች የሚታየው አስተዛዛቢ ነገር ግን መታለፍ የሌለበት ነው:: በርካቶቹ በግንባታ ሰበብ አፀደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይኖራቸው እየተደረጉ ነው:: ሌላው ቀርቶ በቅፅራቸው በዕቃዎችና በጠባብ ሥፍራዎች እንኳን በአበቦችና በሌሎችም ዕፀዋት ለማበጃጀት የሚደረገው ጥረት ደካማ ሆኖ ይታያል:: በግንባታ ተሞልተው አፀዳቸውን ከማጣት ባሻገር የግንባታ ተረፈ ምርቶች ከቅፅረ ቤተ ክርስቲያን በአግባቡ ተፅድቶ እንኳን ባለመውጣቱ በሲሚንቶ ብናኝ፣ በብትን አሸዋ፣ በብሎኬት ስብርባሪ፣ በድንጋይ ሽርፍራፊ፣ በምስማርና ቆርቆሮ ቁርጥራጭ ወዘተ. እዚያና እዚያ ተሞልቶ ሲታይ በእጅጉ ያሳዝናል::

የተተከሉ ተክሎችም እንክብካቤ በማጣታቸው ደርቀው፣ ውበታቸውን አጥተው፣ በሥርዐት ቅርጽና መልክ ተሰጥቷቸው እንዲያድጉ ባለመደረጉም ለትዝብት የሚዳርጉ በርካቶች ናቸው:: ለሆነ ጉባኤ ወይም ለሆነ መልእክት የሚለጠፉ ቢል ቦርዶች/ ባነሮች/ም አንሺ አጥተው ከአገልግሎት ዘመናቸው ውጪ በቅፅረ ቤተ ክርስቲያን ተንጠልጥለው ውበት ሲያደፈርሱ ይታያሉ::

በየፀበል ቦታው የሚጣሉ የውኃ ላስቲኮች የሚያፀዳቸው ጠፍቶ በየቦታው ተንጠባጥበው ማየትም ተለምዷል:: በተለያዩ ምክንያቶች ለጽዳት የዋሉ የሶፍት ቁርጥራጮችም፣ የተለያየ አገልግሎት ሰጥተው አላግባብ የወደቁ የወረቀት ብጭቅጫቂዎችና ፌስታሎችም ወዘተ. በአሳዛኝ ሁኔታ የቅጽሩን ውበት አጉድፈው ስናይ እናዝናለን::

በአግባቡ አገልግሎት የሚሰጡ ሽንት ቤቶች ያሉባቸው፣ ቢኖሩም ተቀልፈው ምእመናንና ሌሎች አገልጋዮችም ለመጠቀም ሲቸገሩ ማየት፤ እንዲሁም አገልግሎት ለመስጠት ክፍት ሆነው ነገር ግን በተከታታይ ንጽሕናቸውን ለመጠበቅ ሥርዓት ያልተበጀላቸው መፀዳጃ ቤቶች የሚፈጥሩት የማይገባ ጠረን ለአፀዱ አካባቢ ከትዝብት በላይ ትዝብት ነው::

ይህ ማለት ግን እግዚአብሔርን በማክበር፣ የሚገባውን በማድረግ፣ ቤተ ክርስቲያንን በአፍአና በውስጥ በነገር ሁሉ የምትስብ ለማድረግ፣ ውበትም፣ ፅዳትም፣ ሥርዓትም እንዲጠበቅ አጥብቀው የሚያገለግሉ የአጥቢያ አመራርና አገልጋዮችም እንዳሉ ሳንዘነጋ ነው::

ሁኖም ቅፅረ ቤተ ክርስቲያን ከየትኛውም የማኅበረሰብ አካባቢዎች ይልቅ በውበቱ፣ በድምቀቱ፣ በመልካም መዓዛው፣ በልጦና ተሽሎ እንዲገኝ ማድረግ የክርስቲያኖች ሁሉ ግዴታ ነው:: ዛፎችን መትከል፣ ጌጠኛ አበቦችን አብዝቶ መንከባከብ፣ ነገሮችን ሁሉ የፀዱና የተስተካከሉ ማድርግ፣ ፍሳሽ ማስወገጃዎችን፣ የቆሻሻ ማከማቻና፣ ማስወገጃ ቁሳቁስና ሥርዓትን መዘርጋት ይገባል::

ጉንፋን እንኳን ተይዘን ወደ ውስጧ ለመግባት የምንጠነቀቅላትን ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አሁን አሁን በሚታዩ መዘናጋቶች ከንቱ ጠረን እንዳይነፍስባት ለማድረግ፣ እንደ አባቶቻችን ንጽሕናዋን መጠበቅ ከምእመናንም ከቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችም የሚጠበቅ ተግባር ነው:: የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳር ለዚህ ሥራ ማስተባበር ከቻለ ቀናነት ከማይለያቸው ምእመናን በጎ ምለሽ እንዳለ ማንም አይጠራጠርም::

# በእውኑ ከአንድ ሰ/ት/ቤት ያሉ እኅቶችና ወንድሞች መጋባት አይችሉምን?

## ክፍል አንድ

*ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች እንደምን ከረማችሁ? ቸርነቱ የማያልቅበት እግዚአብሔር አምላክ የተመሰገነ ይሁንና ይህን ጽሑፍ ወደ እናንተ ለማድረስ አብቅቶኛል። እናም ችግሬን ተጋርታችሁ ለጥያቄዬ የኅሊና ዕረፍት የሚሰጥ መልስ ትሰጡኛላችሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።*

*የክርስትና ስሜ ወለተ መስቀል ይባላል። በ፳፭ ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ እገኛለሁ። በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ውስጥ በሚገኝ አንድ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት ውስጥ እየተማርኩ ነው ያደግሁት። ዩኒቨርሲቲ ገብቼ በድግሪ ተመርቄ አሁን በሥራ ላይ ነኝ። ከዩኒቨርሲቲ ከተመለስኩ በኋላም በአደግሁበት ሰንበት ትምህርት ቤት እያአገለገልሁ ነው።*

*የጥያቄዬም ፍሬ ነገር እንዲህ ነው በማገለግልበት ሰንበት ት/ቤት ውስጥ ከልጅነቴ ጀምሮ በእኅትነትና ወንድምነት የምንተዋወቅ ልጅ የጋብቻ ጥያቄ አቀረበልኝ ። በሰ/ት/ቤታችን ሕግ ደግሞ በአንድ ሰ/ት/ቤት የሚያገለግሉ እኅቶችና ወንድሞች አይጋቡም የሚል ሕግ አለ፤ በሌላ ሰ/ት/ቤት ግን አምስት ስድስት ጥንዶች እርስ በርሳቸው ጋብቻ መፈጸማቸውን አውቃለሁ። በእኛ ሰ/ት/ቤት ደግሞ አንዳንድ ልጆች ለመጋባት ሲፈልጉ የሰ/ት/ቤታችን ሕግ ስለሚከለክላቸው ከሁለቱ አንዱ ሰ/ት/ቤት ይቀይራል፤ ካልሆነም ደግሞ ከሁለቱ አንዱ ከነ አካቴው ከአገልግሎት ይቀራል። በዚህ መልኩም የተጋቡ ብዙ እኅቶችና ወንድሞችን አውቃለሁ። እኔ ደግሞ ለዚህ ብየ እንደ እነርሱ ከአገልግሎት መቅረት ወይም ሰ/ት/ቤት መቀየር አልፈለግሁም። የወንድሜ ፍላጎትና ጥያቄ ደግሞ ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ በመምጣቱ እኔም ተጨንቄያለሁ። በዚህ ምክንያት እሽ ለማለትም እምቢ ለማለትም ጨነቀኝ፤ ለመሆኑ ከአንድ ሰ/ት/ቤት ያሉ እኅቶችና ወንድሞች መጋባት አይችሉምን? በቤተ ክርስቲያን አይጋቡ የሚል ሥርዓት አለ? እሽ ልበለው? ወይስ ወንድሜን አልቀበልም ልበለው ምን ትሉኛላችሁ?*

እኅታችን ወለተ መስቀል በውስጥሽ እየተመላለሰ ያስጨነቀሽንና መፍትሔም አገኝበታለሁ ብለሽ ወደ እኛ ያመጣሽውን ጥያቄ መጻሕፍትን አንብበን አባቶችን ጠይቀን ለመመለስ እንሞክራለን። ነገር ግን በቀጥታ ይህን አድርጊ ይህን አታድርጊ ከማለታችን በፊት ትዳርና ከትዳር ጋር በተያያዘ መታወቅ ያለባቸውን መሠረታዊ ነጥቦችን፣ የሚነሡ ችግሮችንም እናነሣለን። የትዳር ጉዳይ ሲነሣ በዋናነት የፈቃደ እግዚአብሔር፣ የሃይማኖት፣ የፍላጎት፣ የዕድሜ፣ የሥነ ልቡናና የምጣኔ ሀብት ሁኔታዎች ልብ ሊባሉና መሠረታዊ ግንዛቤ ሊያዝባቸው ይገባል። እነዚህንም እንደሚከተለው እናያቸዋለን።

### ሀ. ፈቃደ እግዚአብሔር፦

ኦርቶዶክሳዊ ትዳር በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ በሥጋ ወደሙ የሚመሠረት ክርስቲያናዊ ተቋም ነው። መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ "እኔ የወይን ግንድ ነኝ፤ ቅርንጫፎቹም እናንተ ናችሁ፤ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፣እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል››። (ዮሐ.፲፭፣፭) በማለት እንደ ተናገረ በሕይወት ዘመናችን ልናከናውናቸው ለምንፈልጋቸው ጉዳዮቻችን ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስቀደም መልካም ነው። ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊትም "እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ፤ ቤትን የሚሠሩ በከንቱ ይደክማሉ፤ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ፤የሚጠብቁ በከንቱ ይተጋሉ።" (መዝ.)፻፳፮፣፩) ብሎ እንደነገረን ለሁሉም ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስቀደም ተገቢ ነው።

ለተቻለው በድንግልና፣ በምንኵስና እንዲኖር ላልተቻለው ደግሞ በትዳር ሕይወት እንዲኖር የእግዚአብሔር አምላካችን መልካም ፈቃዱ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ "እግዚአብሔር አምላክም አለ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት" (ዘፍ.፪፣፲፰) ተብሎ ተጽፎ የምናነበውን ሊቃውንቱ ሲተረጒሙት አዳም ለሰባት ቀናት ያህል ብቻውን ነበረ፤ በዚህ ጊዜ ሌሎችን ፍጥረታት ጥንድ ጥንድ ሆነው ተመለከተ፤ የእርሱ ብቸኝነት ግን አሳሰበው። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር አምላክ የሰውን ብቸኝነት አልፈቀደምና ለአዳም ሔዋንን አስገኘለት። ስለዚህ እኅታችን ለአዳም ሔዋንን ያስገኘ ለአንቺም የአንቺ የሆነውን አዳምን እንዲሰጥሽ እግዚአብሔርን መለመን ተግቶ መጸለይ ያስፈልጋል።

### ለ. ከፍላጎት አንጻር

ትዳር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በሁለቱ ማለትም በወንዱና በሴቷ መፈላለግ የሚፈጸም ነው። ከላይ በተመለከትነው የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ የአዳም ፍላጎት፣ የእግዚአብሔርም መልካም ፈቃድ በግልጽ ተስተውሏል። አንቺንም የጠየቀሽ ወንድም ፍላጎቱን ገልጦልሻል፤ አንቺም ብትሆኝ በሰንበት ትምህርት ቤት ያለው ሕግ አስጨንቆሽ እንጂ ፍላጎቱ እንዳለሽ ጥያቄሽን ከአነሣሽበት አንጻር መረዳት ይቻላል። የወንድማችን ፍላጎት ካለ፣ የአንቺም ፍላጎት ካለ፣ በዋናነት ለእኛ ለሰዎች ያልተገለጸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። እርሱን ደግሞ ተግቶ በመጸለይ በትዕግሥት መጠበቅ ያስፈልጋል። ነቢዩ

ዳዊት “እግዚአብሔርን በትዕግሥት ደጅ ጠናሁት፤ እርሱም ተመልሶ ሰማኝ፤ የልመናዬንም ቃል ሰማኝ” (መዝ.፴፱፥፩) ብሎ እንደነገረን ተግቶ መጸለዩና በትዕግሥት መጠበቁ ለጥያቄያችንና ለጭንቀታችን ሁሉ ዘላቂ መፍትሔ እንደሚያስገኝልን ያስረዳናል።

በእግዚአብሔር ፈቃድ ለይስሐቅ ሚስት ትሆነው ዘንድ በአባቱ ሎሌ አማካይነት የተገኘችው ርብቃ ለይስሐቅ ሚስት እንድትሆን ስትፈለግ የእርሷ ፈቃድ ተጠይቆ ነው። በአብርሃም ሎሌና በርብቃ ቤተ ሰቦች መካከል የነበረውን ውይይት በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ያስረዳናል። “እግዚአብሔር መንገዴን አቅንቶልኝ ሳለ አታዘግዩኝ፤ ወደ ጌታዬ እሄድ ዘንድ አሰናብቱኝ አላቸው። እነርሱም ብላቴናይቱን እንጥራና ከአፍዋ እንጠይቅ አሉ። ርብቃንም ጠርተው ከዚህ ሰው ጋር ትሄጃለሽን? አሉአት። እርሷም አዎን እሄዳለሁ አለች።” (ዘፍ.፳፬፥፶፮-፶፰) ስለዚህ ትዳር በእግዚአብሔር ፈቃድ በሁለቱ ተጋቢዎች ፍላጎት የሚፈጸም መሆኑን እንረዳለን። በፍትሐ ነገሥትም “ቤተ ሰቦቿ የመረጡት እጮኛና እርሷ ልጅቱ የመረጠችው እጮኛ በወገንም በሞያም ትክክል ቢሆኑ በእርሱ ላይ የሚደረግ የሴቲቱ ፈቃድ ይሁን” (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳ ቍጥር ፱፻፰) የሚል ትእዛዝ እናገኛለን። ስለዚህ ለበጎ ነገር መፈላለግ መልካም ነውና የሁለታችሁም ፍላጎት መኖሩ ወሳኝ ነገር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

### ሐ. ከዕድሜ አንጻር

ለትዳር ወሳኝ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ ዕድሜ ነው። በሥነ ፍጥረት ታሪክ እንደሚነገረው እግዚአብሔር አምላክ በአርአያውና በአምሳሉ የፈጠረው አዳም የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ፣ ሔዋን ደግሞ የዐሥራ አምስት አመት ወጣት ሆነው ነው የተፈጠሩት። ይህ ማለት ለትዳር የሚያበቃ የሰውነት ክፍል ያለው/ ያላት ማለት ነው። በፍትሐ ነገሥትም “ዕድሜዋ ፳፭ ዓመት ያህል ቢሆን እንደወደደች ልታገባ በራሷ ሥልጣን አላት።” (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፬ ቍጥር ፶፮–፶፰) ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን። ይህ የሚያስረዳን ዕድሜ ለትዳር ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ነው። ይህ የዕድሜ ጉዳይ ሳይደርስና ብስለት ሳይኖር ቢፈጸም ምን አልባት በጾታዊ ተግባር አለመጣጣም ከዚህም አልፎ ለሌላ በሽታ መጋለጥም ሊኖር ይችላል። ሰንበት ትምህርት ቤቶችም ብዙ ጊዜ በሰ/ት/ቤትሽ እንደጠቀሰሽው ዓይነት ሕግ እንዲያወጡ የሚያስገድዳቸው ሕፃናት በእግዚአብሔር ቃል ሊያድጉ በሚችሉበት የዕድሜ ደረጃ ወደዚህ ተግባር እንዳይገቡ ሊሆን ይችላል።

አንዳንድ ችግሮችም በራሳቸው ብቻ አያቆሙም ሌላ ተጨማሪ ችግርም ይዘው ይመጣሉ። ስለዚህ ያለዕድሜ ወደ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ተግባር ይገቡና አንድ ከላይ እንደ ተጠቀሰው የጤና ችግር ይፈጠራል፤ ሁለት የጾታዊ ተግባር አለመጣጣም ይኖርና ጉዳዩ ከጸጋነት ውጪ ይሆናል። ከዚህ ባለፈ ግን በጊዜው ሊይዙት የሚገባቸውን ትምህርት፣ ሃይማኖታዊ ብስለት፣ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት፣ ጣዕም፣ ጸጋና በረከት ያጣሉ። ከዚህም አልፎ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በመተላለፋቸው ከመንግሥተ ሰማያት ይወጣሉ።

### መ. ከሃይማኖት አንጻር

ምንም እንኳን ጋብቻ ሲታሰብ የሥጋ ፈቃድ ተደርጎ የሚታሰብ ቢሆንም ቅሉ እግዚአብሔር የፈቀደውና ሰውም ይበዛበት ዘንድ አምላካዊ ጥበቡ የሚገለጽበት ስለሆነ ተጋቢዎች በሃይማኖታቸው አንድ መሆን መብሰል አለባቸው። መንፈሳዊ ትዳር ታላቅ ተቋም ሲባል ይህን በአግባቡ ለመምራት ይቻል ዘንድ ሃይማኖታቸውን በሚገባ ማወቅ ብቻም ሳይሆን እርስ በእርሳቸውም በሃይማኖት አንድ መሆናቸውን መረዳት፣ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርትም እንዲሁ በአግባቡ መረዳት ይኖርባቸዋል።

በሃይማኖት ከመብሰል ጋር ሁለቱም የአንድ ሃይማኖት ተከታይ መሆን አለባቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ምንም እንኳን አንድነትን የሚያበረታ ትምህርት ቢያስተምርም አንድ የማይሆኑ ነገሮችን ግን አንድ ማድረግ እንደሌለብን በአጽንኦት አስተምሯል። ለምሳሌ፡- ለቆሮንቶስ ምእመናን በላከው መልእክቱ “ተጠራጣሪዎች አትሁኑ፤ ወደማያምኑ ሰዎች አንድነትም አትሂዱ፤ ጽድቅን ከኃጢአት ጋር አንድ የሚያደርጋት ማን ነው? ብርሃንንስ ከጨለማ ጋር የሚቀላቅል ማን ነው? ክርስቶስን ከቤልሆር ጋር አንድ የሚያደርገው ማን ነው? ወይስ ምእመናንን ከመናፍቃን ጋር አንድ ወገን የሚያደርጋቸው ማን ነው? የእግዚአብሔርን ታቦትስ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው? የሕያው እግዚአብሔር ማደሪያዎች እኛ አይደለንምን? እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተናገረ ‹‹እኔ በእነርሱ አድራለሁ፤ በመካከላችውም እኖራለሁ፤ አምላካቸውም እሆናቸዋለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆኑኛል።›› ስለዚህ ከመካከላቸው ተለይታችሁ ውጡ፤ ከእነርሱም ተለዩ፤ ወደ ርኵሳን አትቅረቡ፤ እኔ እቀበላችኋለሁ። አባት እሆናችኋለሁ፤ እናንተም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ትሆኑኛላችሁ አለ ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር” (፪ቆሮ. ፮፥፲፬-፲፰) በማለት ማን ከማን ጋር አንድ መሆን እንዳለበትና ማን ከማን ጋር አንድ መሆን እንደሌለበት ያስረዳል።

በፍትሐ ነገሥትም “በትሩፋቱ ላይ እንደሚጨምር ሁሉ ምእመን የእርሱ ወገን ያልሆነችውን፣ አማኝ ያልሆነችውን ማግባት እንዳይገባ ይናገራል” (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፳፬፥፰፻፶፮) የእርሱ ወገን ያልሆነችውን የሚለው በሃይማኖት እንጂ ዛሬ ትውልዱ እየተተራመሰበት ባለው በዘር፣ በጎሣ፣ በቀለም ወዘተ. ለማለት አይደለም። ቤተ ክርስቲያን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አምኖ የተጠመቀውን ሁሉ የአንድ አባት፣ የአንድ እናት ልጅ ብላ ነው የምታስተምረውና የእርሱ ወገን የሚለውን በሃይማኖት የምትመስለውን ለማለት እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል። ስለዚህ ሁለቱ ተጋቢዎች በሃይማኖት አንድ መሆን አለባቸው ከተባለ ከአንድ ሰንበት ትምህርት ቤት ያሉ ወንዶች ሴቶች ቢጋቡ ምን ችግር አለው የሚለውን ጥያቄ ማንሣት ተገቢ ነው።